# የዮሐንስ ወንጌል ጥናት(34)

## ጥናት አንድ ዮሐንስ 1፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ልጅ እና የእርሱ ቤተሰብ ውስጥ ለመቀላቀል የሚያስፈልገው አንድ ነገር ቢኖር ኢየሱስን መቀበልና በስሙ ማመን ብቻ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ወደ ራሱ ወገኖች መጣ፤ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፤ ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሄር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው፡፡›› ዮሐ 1፡12

1. የዮሐንስ ወንጌል 1፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ስለኢየሱስ አመጣጥ ለመናገር የጀመረበት መንገድ ከሌሎቹ ወንጌሎች ጋራ በማነጻጸር ተናገር፡፡ ዮሐንስ ከፍጥረት በፊት ስለነበረው ስለየሱስ ለመናገር‹‹በመጀመሪያ›› ማለቱ ከየትኛው መጽሃፍ ጋራ ያመሳስለዋል?
2. ቁ3-5 ስናነብ በተለይ ቁ3 ኢየሱስን እንደ ምን አድርጎ ነው የሚያስቀምጥልን? በእርሱ ያልተፈጠረ ነገር ምን ታያለህ?
3. ዮሐንስ በቁ6-7 ላይ ስትመለከት መልዕክተኛነቱ ለማን ነው? ተልዕኮውስ ምን ነበረ? በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ኢየሱስ የተናገረውን ንግግር በመውሰድ ራስህን ከዮሐንስ ጋራ በማነጻጸር ተናገር፡፡
4. ቁ4-9ን ስናነብ ተደጋግሞ የተጠራው አንድ ነገር ምን የሚል ነው? በነዚህ ክፍሎች ስንት ጊዜ ተጠቅሷል? ስለኢየሱስ ማንነት ቁ9 የሚነግረን ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? አንተስ በጨለመው ህይወትህ የኢየሱስ እውነተኛ ብርሃን በርቷ ወይ?
5. ቁ13 ላይ ‹‹እነዚህ›› እያለ የሚናገርላቸው ሰዎች የትኞዎቹ ሰዎች ናቸው? በዚህ ቁጥር ላይ የምናነበው ከእግዚአብሄር መወለድ የሚለው አስተሳሰብ በዮሐ 3፡3 ላይ ኢየሱስ ራሱ ከተናገረው ነግግር ጋራ ኢንዴት እንደሚመሳሰል አስረዳ፡፡
6. ዮሐ በቁ1-2 ላይ ዮሐንስ ማረጋገጥ የፈለገው ነገር ምን ነበረ? በቁ14 ላይስ ማረጋገጥ የፈለገው እውነት ምንድነው? ጸሐፊው የኢየሱስን ክብር እንዳየ ሆኖ ሲናገር እናየዋለን፡፡ መቼ ይመስልሃል ዮሐንስ የእርሱን ክብር የተመለከተው?
7. ቁ15-18 ውስጥ በተለይ ቁ17 በብሉይ ኪዳን ህግ ወይም እውነት ብቻ እንጂ ጸጋ የሚባል ነገር አልነበረም ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው? ‹‹በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀብለናል›› ስል ምን ያመለክተናል? ይህንን የመሰለ የተትረፈረፈ ጸጋ እንደተቀበልክ ትረዳለህ ወይ?
8. ቁ10-12 በዚህ ክፍል መብት የተሰጣቸው ሰዎች እነማን ናቸው? የተሰጣቸው መብት ምን እንደሆነ አብራርተህ ተናገር፡፡ የእግዚአብሄር ልጅ የመባልን መብት አግኝተሃል ወይ? የእግዚአብሄር ልጅና የእርሱ ቤተሰብ ለመሆን ኢየሱስን ማመንና እርሱን መቀበል እንደሚያስልግህ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሁለት ዮሐንስ 1፡19-34

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ያየንና ያመንን ሁላችን፤ ሌሎች ደግሞ የኢየሱስን ማንነት እንዲያዩና እንዲያምኑበት የመመስከር ሀላፊነት እንዳለብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አይቻለሁ፤ እርሱ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እመሰክራለሁ፡፡›› ዮሐ 1፡34

1. የዮሐንስ ወንጌል 1፡19-34 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ19 ላይ ስለ ዮሐንስ ጥያቄ የነበራቸው ሰዎች እነማን ነበሩ? የነዚህ ሰዎች ጥያቄ ምን ነበረ? በመልዕክተኛነት ሲያገለግሉ የሚታዩት ሰዎች እነማን እንደነበሩ ተናገር፡፡
2. በቁ20-23 ላይ ዮሐንስ አንድ አስረግጦ የተናገረው እውነት ምን ነበረ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሌሎች የተጠየቃቸው ሶስት ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው?
3. ከእነዚህ ሰዎች ለቀረበለት ጥያቄ የዮሐንስ መልስ በቁ23 መሰረት ምን ነበረ? ማቴ 11፡7-9 ኢየሱስ ስለ ዮሐንስ የተናገረውንና፤ ዮሐንስ በዚህ ክፍል ስለራሱ የሰጠውን ምስክርነት ስትመለከት ስለ ዮሐንስ ባህርይ ምን ትማራለህ? ዛሬ ኢየሱስ በዮሐንስ ቦታ ስአንተ ቢናገር የሚናገረው ነገር አንተ ስለራስህ ከምትናገረው ጋራ ቢነጻጸር ምን ይመስል ይሆን? ራስህን ጠይቅ፡፡
4. ቁ24-27 ላይ ለዮሐንስ የቀረበለት ሌላው ጥያቄ ምን ነበረ? የዚህኛው ጥያቄ መንስሄ ወይም መነሻ የሆነውስ ነገር ምንድ ይመስልሃል?
5. ቁ26-28 ትን ከማር 1፡8 ጋራ በማገናዘብ የዮሐንስ አጭር መልስ ምንድነው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተለይ ኢየሱስን አስመልክቶ የሰነዘራቸውን ሃሳቦች ሁሉ ለመዘርዘር ሞክር፡፡ ይህ ሁሉ ውይይት የተካሄደው የት ሥፍራ ነበረ?
6. በቁ29 ላይ ዮሐንስ ኢየሱስን ያስተዋወቀው ምን በማለት ነበረ? ራዕይ 5፡5 ላይ ያለውን የስሙን ስያሜ በማገናዘብ እነዚህ ሁለት ዓይነት ስያሜዎች ለኢየሱስ ምን ማለት እንደሆኑ አስረዳ፡፡ ለአንተ ኢየሱስ የትኛው ነው በግ፣ አንበሳ ወይስ ሁለቱንም?
7. በቁ30 ላይ ኢየሱስ ከዮሐንስ በፊት እንደነበረ ይናገርለታል፤ ነገር ግን ሉቃስ 1፡35-37 ትን ስናነብ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ቢያንስ በስድስት ወር እንደሚበልጠው እንመለከታለን፤ ታዲያ ዮሐንስ ይህንን ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
8. በቁ32-34 ውስጥ ማየት የሚለውን ሃሳብ ስንት ጊዜ ተጠቅሶ ታየዋለህ? ዮሐንስ በተለይም በቁ34 ላይ የግል ውሳኔ አድርጎ የሚናገረው ሃሳብ ምንድነው? አንተስ፤ የኢየሱስን ማንነት ያየህና የቀመስክ ከሆነ ስለ እርሱ ለመመስከር ምን ያህል ቁርጠኛ ውሳኔ አድርገሃል?

# ጥናት ሶስት ዮሐንስ 1፡35-51

የጥናት ዓላማ፡- እንደ እንድርያስ ሰዎችን ፈልጎ በመሄድ ስለ ክርስቶስ መመስከር እንዳለ ሁሉ፤ እንደ ፊሊጶስ ደግሞ እግዚአብሄር በህይወታችን ለሚያመጣቸው ሰዎች አጋጣሚውን በመጠቀም ስለጌታ የሱስ አዳኝነት መናገር እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እንድርያስ በመጀመሪያ ያደረገው ወንድሙን ስምዖንን ፈልጎ መሲሁን አገኘነው ብሎ መናገር ነው…ፊሊጶስ ናትናኤልን አግኝቶ…የናዝሬቱ ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው፡፡›› ዮሐ 1፡41፣ 45

1. የዮሐንስ ወንጌል 1፡35-51 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ35-37 ላይ ዮሐንስን ከስንት ደቀመዛሙርቱ ጋራ ነው የነበረው? ከዮሐንስ ደቀመዛሙርት ወደ ኢየሱስ የሄዱት ስንቶቹ ናቸው? ይህንን ለማድረግ ደቀመዛሙርቱን ያነሳሳቸው ዋነኛ ነገር ምን ነበረ?
2. ዮሐንስ ስለየሱስ እየተናገረ ደቀመዛሙርቱን ማጣቱ ምን ዓይነት ስሜት የሚፈጥርበት ይመስልሃል? በእርሱ አገልግሎት ከውድድር ይልቅ መታዘዝ ጎልቶ ይታያል ማለት የሚቻለው በምን መንገድ ነው? አንተስ ሰዎች ላንተ የማይገባህን ክብር ሊሰጡህ ሲሞክሩ ምላሽህ ምን ይሆን?
3. ከቁ40-42 እንደምንመለከተው ኢየሱስን አስቀድሞ መከተል የጀመረው ደቀመዝሙር ማን ይባላል? ኢየሱስን ከተገናኘ በኋላ ያደረገው የመጀመሪያ ነገር ምን ነበረ?
4. ቁ42-44ትን ስታነብ የእንድርያስ ወንድም ስንት መጠሪያዎች አሉት? ማን ማን ተብሎ ሊጠራ እንደሚችል ተናገር፡፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ኢየሱስን ከተከተሉት ሰዎች ከቤተ ሳይዳ የነበሩት እነማን ናቸው?
5. ፊሊጶስ ስለ ኢየሱስ ምስክርነቱ ለናትናኤል የተናገራቸው ቢያንስ ሶስት እውነቶችን ዘርዝር፡፡ ከነዚህ ሁሉ ለናትናኤል ጥያቄ የፈጠረበት የትኛው ሃሳብ ነበረ? ቁ47 ከእርሱ አነጋገር እንደምንረዳው የኢየሱስን መምጣት የተመለከተው እንደምን ነበረ ማለት እንችላለን?
6. ቁ47-50 ላይ ናትናኤል ከኢየሱስ ጋራ ባደረገው ውይይት የደረሰበት መደምደሚያ ሃሳብ ምን ነበረ? ናትናኤልን ወደዚህ ዓይነት የማያወላውል ውሳኔ ያደረሰው ሃሳብ ምን ይመስልሃል?
7. በቁ45 ‹‹ፊሊጶስ ናትናኤልን አግኝቶ›› ቁ41 ደግሞ ‹‹ወንድሙን ስምዖንን ፈልጎ›› የሚሉ አነጋገሮችን እንመለከታለን፡፡ በፊሊጶስና በእንድርያስ ምስክርነቶች መሃል ጎልቶ የሚታየው አንድ ልዩነት ምንድነው ተላለህ? ከነዚህ ሁለት ሰዎች የምስክርነት ዓይነት ምን ትማራለህ? እቅድ በማድረግ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሁኔታዎች ሲገኙ እድል በመጠቀም፤ በሁለቱም መንገድ ስለጌታ መናገርህን አትተው፡፡

# ጥናት አራት ዮሐንስ 2፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- አለኝ የምንላቸው ማንኛቸውም ዓይነት ጥሩና መልካም ሆነው የሚታዩን ነገሮቻችን ሁሉ፤ ኢየሱስ ከሚሰጠው ነገር ጋራ ሲወዳደር እንደ መናኛ ነገር ሆኖ እንደሚቆጠር ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሰው ሁሉ በመጀመሪያ የሚያቀርበው ጥሩውን የወይን ጠጅ ነው፡፡ እንግዶቹም ብዙ ከጠጡ በኋላ መናኛውን የወይን ጠጅ ያቀርባል፤ አንተ ግን…›› ዮሐ 2፡10

1. ዮሐ 2፡1-11 በአንድነት ይነበብ፡፡ በእነዚህ አስራ አንድ ቁጥሮች ውስጥ በተለያየ መንገድ ማንነታቸው የተጠቀሱትን ሰዎች ሁሉ ዘርዝር፡፡ በዮሐንስ አነጋገር በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናየው ሰርግ የተካሄደው መቼ ነበረ?
2. ኢየሱስ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ተአምር አድርጎ አያውቅም፤ ታዲያ ማርያም በቁ3 ላይ ሰርገኞቹ የሚገኙበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ወደ እርሱ ያመጣችው ምን አስባ ይመስልሃል?
3. በቁ4 ላይ ኢየሱስ ‹‹አንቺ ሴት›› የሚለውን አባባል እናቱን እንዳላከበራት አድርገው አንዳንዶች ይናገራሉ፡፡ ዮሐ 19፡26 ትን 20፡15 ስትመለከት ይህ አነጋገሩ ለአንተ ምን ማለት ይመስልሃል?
4. ማርያም በዚህ ክፍል ኢየሱስ እንዳቃለላት ወይም እንዳዋረዳት ሆኖ እንደተሰማት የሚጠቁመን ነገር አለ ወይ? በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማርያም ከኢየሱስ የኢየሱስን መልስ ከሰማች በኋላ የተናገረችው ነገር ምን ነበረ? ለማርያም አክብሮት አለኝ የሚል ሰው ከዚህ ክፍል አንጻር ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?
5. ኢየሱስ ለአገልጋዮቹ የሰጠው የመጀመሪያ ትዕዛዝ ምን ነበረ? አገልጋዮቹ ማርያም የነገረቻቸውን በሚገባ ሰምተዋታል ማለት የምንችለው ለምንድነው?
6. የኢየሱስ ሁለተኛው ትዕዛዙ ለአገልጋዮቹ ምን ነበረ? ለዚህ ትዕዛዙስ የአገልጋዮቹ ምላሽ ምን ነበረ? ከእነዚህ አገልጋዮች ልንማር የምንችለው አንድ ትልቅ ትምህርት ምንድነው ትላለህ?
7. ቁ11ን ስናነብ ኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምራቱን ያደረገው በምን ዓይነት ስፍራ ተገኝቶ ነበረ? በሰርጉ ላይ የተገኙት በሙሉ በእርሱ ያመኑ ናቸው ብለህ ትገምታለህ ወይ? ኢየሱስ በእንደዚህ አይነት ስፍራ ከተገኘ ለእኛ ሊያስተላልፈው የሚገባው መልእክት ምን ሊሆን ይገባል ትላለህ?
8. በቁ10 ላይ የድግሱ ሃላፊ አስቀድመው አዘጋጅተውት ላለቀባቸውና፤ አሁን ደግሞ ኢየሱስ ለሰጣቸው አዲስ የወይን ጠጅ መጠሪያ አድርጎ የተጠቀመባቸው ቃላት ምን ነበሩ? ሰርገኞቹ ስንት ጊዜ የደከሙበት ወይን ጠጅ ኢየሱስ ከሰጣቸው ጋራ ሲነጻጸር መናኛ እንደሆነው ሁሉ፤ አንተስ ህይወትን ያለ ኢየሱስ በራስህ እየደከምክ ይሆን ወይ? ብዙ ደክመህ ከምታገኘው፤ ከእርሱ የምትቀበለው እንደሚበልጥ አትዘንጋ፡፡

<u>ጥናት አምስት ዮሐንስ 2፡12-25</u>

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ቃል የሚናገረውን እውነት የማይጨምር፤ በተአምራትና በድንቅ ላይ ብቻ የተመሰረተ እምነት አስተማማኝነትና ዘላቂነቱ የሚያጠያይቅ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ብዙ ሰዎች ያደረገውን ተአምራት አይተው በስሙ አመኑ፤ ኢየሱስ ግን ሰውን ሁሉ ስለሚያውቅ አይታመንባቸውም ነበር›› ዮሐ 2፡23-24

1. ዮሐ 2፡12-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ13-16 ላይ ኢየሱስ በቤተመቅደስ ውስጥ ያጋጠመው ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስ በዚህን ጊዜ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ?
2. በነዚህ አራት ቁጥሮች ውስጥ የኢየሱስን ‹‹አባረረ››፣ ‹‹በተነ››፣ ‹‹ገለበጠ››፣ ‹‹አስወጣቸው›› የሚሉትን አነጋገሮች ስናይ ኢየሱስ ስለተሰማው ስሜት ምን መናገር እንችላለን? ይህንን ከባድ እርምጃ ስለወሰደበት ምክንያት ከክፍሉ ምን መረዳት እንችላለን? የዚህ አይነቱ ድርጊት በእኛ ዘመን በቤተ ክርስትያን ሊከሰት የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ተወያዩባቸው፡፡
3. ይህንን ኢየሱስ ያደረገውን ነገር ማየታቸው ደቀ መዛሙርቱን የጠቀማቸው ይመስልሃል ወይ? አስረዳ፡፡ ይህ ድርጊት ለአይሁድስ ትምህርት ሰጥቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ፡፡
4. በቁ20-22 ላይ የአይሁድ ጥያቄ ምን ነበረ? ከዚህ ክፍል ስንመለከት በአይሁድና የኢየሱስ አነጋገር ሊገባቸው ያልቻለበት ምክንያት ለምን ነበረ?
5. ኢየሱስ የተናገረውን ነገር ደቀ መዛሙትቱ ከአይሁድ በተለየ መንገድ የተረዱት ይመስልሃል ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ በቁ22 መሰረት ደቀ መዛሙርቱ ‹‹አመኑ›› ሲል ያመኗቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ነበሩ?
6. በቁ23-25 ላይ በኢየሱስ ሲያምኑ የምናያቸው ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ሰዎች ስላመኑበት ምክንያት ከነዚህ ቁጥሮች ምን እንረዳለን? አነዚህ ተአምራቱን አይተው ስላመኑት ሰዎች ኢየሱስ የነበረው አመለካከት ምን ይመስላል?
7. በቁ22 ላይ ያመኑት ሰዎችና በቁ23 ላይ ያመኑት ሰዎች እምነታቸውን ከምን እንደመነጨ የምትረዳውን ተናገር አስረዳ፡፡ እነዚህን ሁለቱን ስትመለከት ከሮሜ 10፡17 ጋራ የሚዛመደው የትኛው ነው ብለህ ታምናለህ? እምነታችን የተመሰረተው በተአምር ላይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሄርን ቃል በእምነት እንዳለ የተቀበልነው መሆናችንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት ስድስት ዮሐንስ 3፡1-21

የጥናት ዓላማ፡- በጌታ በየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሰው ከእግዚአብሄር ፍርድ እንዳመለጠና፤ በእርሱ ያላመነ ሰው ግን አሁንም ገና ከእግዚአብሄር ፍርድ በታች እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሄር ልጅ ስም ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል፡፡›› ዮሐ 3፡18

1. ዮሐ 3፡1-21 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ውስጥ ስንመለከት ኢየሱስን ሊያነጋግር የመጣው ሰው በምን ሰዓት ላይ ነበረ? ስለሚያነጋግረው ሰው የምናውቃቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ይህ ሰው ስለ ኢየሱስ የነበረው አመለካከት ምን ይመስል ነበረ?
2. በቁ3-4 ላይ የነበረው አዲስ የውይይት አጀንዳ ምን ነበረ? በዚህ ውይይት ላይ ኢየሱስና ኒቆዲሞስ የተላለፉበት ሃሳብ ምንድነው ትላለህ?
3. በተለይ የኒቆዲሞስን ማንነት ስንመለከት የኢየሱስን ንግግር ለመረዳት መቸገሩ ሊያስገርመን የሚችለው ለምን ይመስልሃል? ይህ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያለውና የተማረ ሰው መረዳት ያልቻለውን እውነት ብዙዎች ሀሁ ያልተማሩ ሰዎች መረዳት እንዲችሉ የሆነው ከምን የተነሳ ነው?
4. ቁ9-10 ላይ ኢየሱስ የኒቆዲሞስን ጥያቄ የመለሰው በምን መንገድ ነበረ? ኢየሱስ ሲናገር ቁ3 ና ቁ5 ‹‹ማንም››፣ ቁ15 ደግሞ ‹‹ሁሉ›› እያለ ይናገራል፡፡ ይህ አዲስ የመወለድ ነገር የሚመለከተው ማንን እንደሆነ ነው የሚያሳየን?
5. በቁ14-15 ላይ ሙሴ በዘሑ 21፡7-9 ባደረገውና፤ በኢየሱስ ሞት መሃል ያለውን ግንኙነት አስረዳ፡፡
6. ቁ16ን ስናነብ እግዚአብሄር ለሰው ልጆች ያለውን የፍቅሩን መጠን ማረጋገጥ የቻለው እንዴት ነበረ? ቁ17 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተልዕኮ ምን ይነግረናል? ይህ ቁጥር ተልዕኮው ስላልነበረውስ ነገር የሚነግረን ምንድነው?
7. በቁ19-21 ላይ ተደጋግሞ የተነገረው አንድ ቃል ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ይህንን ቃል ስንት ጊዜ እናገኘዋለን? ይህንን ቃልና የእግዚአብሄርን ፍርድ የሚያገናኘው ሃሳብ ከክፍሉ መሰረት ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡
8. በቁ18 ላይ ያለውን ሃሳብ ስንመለከት፤ ከእግዚአብሄር ፍርድ የሚያመልጡት ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? በክርስቶስ ያመንክ ከሆን ሮሜ 8፡1 እንደሚናገረው ኩነኔ እንደሌለበት ሰው ትመላለሳለህ ወይ? በስሙ ያላመንክ ከሆነ ግን ከእግዚአብሄር ፍርድ ማምለጫው መንገድ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ስለሆነ በእርሱ አምነህ ከፍርድ አምልጥ፡፡

# ጥናት ሰባት ዮሐንስ 3፡22-36

የጥናት ዓላማ፡- እኛ አማኞችን ደስ ሊያሰኘን የሚገባው አንድ ነገር ቢኖር፤ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጥተው በእርሱ መታነጻቸው እንጂ፤ ከእኛ ጋራ ወይም ደግሞ ከእኛ ቤተ ክርስትያን ጋራ ያላቸው ግንኙነትና መያያዝ ሊሆን እንደማይገባው ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሙሽራይቱ የሙሽራው ነች፤ ድምጹን ለመስማት በአጠገቡ የሚቆመው ሚዜ ግን የሙሽራውን ድምጽ ሲሰማ እጅግ ደስ ይለዋል፤ ያ ደስታ የእኔ ነው እርሱም አሁን ተፈጽሟል፡፡›› ዮሐ 3፡29

1. ዮሐ 3፡22-36 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ22-24 ስናነብ ኢየሱስ ምን ሲያደርግ ነው የሚገኘው? ዮሐንስስ? በዚህ ሥፍራ የምናነበው ነገር ስለተፈጸመበት ጊዜ ክፍሉ ምን ይነግረናል?
2. ከቁ26 ጀምሮ የምናነበው ሃሳብ መንስዔው ምን ነበረ? ሰዎቹ የኢየሱስን ማንነት ለዮሐንስ የገለጡት በምን መንገድ ነበረ? በእነዚህ ሰዎች አመለካከት ለዮሐንስ ችግር አድርገው የሚያዩት ነገር ምን ነበረ?
3. ቁ27ትን በማንበብ የዮሐንስ መልስ በአጭሩ ምን የሚል እንደነበረ አስረዳ፡፡ ይህ ሰው አስቀድሞ ለህዝቡ በማያሻማ መንገድ ግልጽ አድርጎ የነገራቸው ነገር ምን ነበረ?
4. ‹‹ኢየሱስ እየበለጠህ እኮ ነው ምን ትጠብቃለህ›› ለሚለው የሰዎቹ ሃሳብ በቁ30 ዮሐንስ ምን አለ? ለአንተስ የኢየሱስ ከፍ ማለትና የአንተ ደግሞ ዝቅ ማለትህና መዋረድ ምን ያህል ከልብህ ትመኘዋለህ?
5. በአውደ ምንባቡ መሰረት በቁ29 ላይ ሙሽራ ተብላ የተጠራቸው ማንነች ትላለህ? ሙሽራውስ? ‹‹ሙሽራይቱ የሙሽራው ነች›› ከሚለው አነጋገር የምትረዳው ምን እንደሆነ ለወገኖች አካፍል፡፡
6. በቁ31 መሰረት ከላይ የመጣ የሚለውን ከማን ጋራ ነው የሚያወዳድረው? ማን ነው በልጦ የሚገኘው? ከሰማይ የመጣው የሚበልጥበት ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው ነገር ምንድነው?
7. ቁ36ትን ስታነብ ህይወትን የማያየው ሰው ማን ነው ይላል? የዘለዓለም ህይወት አለው የተባለለት ሰውስ ማን ነው? ከነዚህ ከሁለት አይነት ሰዎች አንተ ራስህን ከየትኛው ትመድባለህ?
8. በቁ26 ላይ ‹‹…ሰውም ሁሉ ወደእርሱ እየሄደ ነው፡፡›› በማለት የተናገሩት ሰዎች ከዮሐንስ የጠበቁት መልስ ምን ይመስልሃል? ዮሐንስ በ29 ላይ ‹‹ሚዜ ግን የሙሽራውን ድምጽ ሲሰማ እጅግ ደስ ይለዋል፤ ያ ደስታ የእኔ ነው፤ እርሱም አሁን ተፈጽሟል፡፡›› ብሎ ከመለሰው መልስ ምን መማር እንችላለን? አንተን ደስ ሊያሰኝህ የሚገባው ነገር ሰዎች ወደ ሙሽራው ኢየሱስ መጠጋታቸው እንጂ አንተ ወዳለህበት ቤተ ክርስትያን መቀላቀላቸው ስላልሆነ በዚህ ላይ ያለህን አመለካከት መርምር፡፡

# ጥናት ስምንት ዮሐንስ 4፡1-26

የጥናት ዓላማ፡- ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ማወቅ መልካም ነገር እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም፤ የበለጠውና ሰዎችን ለዘለዓለም ህይወት የሚያበቃው ግን ከእርሱ ጋራ በግል መተዋወቅ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሴትየዋም ክርስቶስ የተባለ መሲህ እንዲመጣ አውቃለሁ…ኢየሱስም የማነጋግርሽ እኮ እኔ እርሱ ነኝ ሲል ገልጦ ነገራት፡፡›› ዮሐ 4፡26

1. ዮሐ 4፡1-26 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 መሰረት ፈሪሳውያኑ የደረሳቸው ዜና ምን ነበረ? ዜናው ትክክለኛ ነበረ ወይ? ለምን?
2. ቁ4-9 ስታነብ ኢየሱስ ሰማርያ ከተማ የገባው ለምንድነው ትላለህ? በሳምራይቱ ሴትና በኢየሱስ መሃል ውይይቱ የተካሄደበት ከተማ ስም ማን ይባላል? ስለዚህች ከተማ ከክፍሉ ምን የምናውቀው ነገር አለ?
3. በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ስንመለከት ውይይቱን የከፈተው ማን እንደነበረና ውይይቱ በምን እንደተጀመረ ተናገር፡፡ ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ ከሳምራዊቷ ሴት አመላለስ ስለሁለቱ ህብረተሰቦች ምን መረዳት እንችላለን?
4. በ7-15 ያሉት ቁጥሮች ያተኮሩበት አንድ ቃል ምንድነው? ይህንን ቃል በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንት ጊዜ ተጠቅሶ ታየዋለህ? ኢየሱስ ይህንን ያህል ሰፋ ያለ ጊዜ በዚህ ቃል ዙሪያ ማጥፋት የፈለገ ይመስልሃል?
5. ኢየሱስ በተለይም በቁ10-11 ላይ ይህች ሴት እንዳላወቀችና እንዳልተረዳች የሚናገራቸው ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? ይህች ሴት የህይወት ውሃ ከየት እንደሚገኝ ነው የምታስበው? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
6. 13-15 መሰረት ከጉድጓዱ በሚወጣው ውሃን ኢየሱስ በሚሰጠው ውሃ መሃል ስላለው ልዩነት ኢየሱስ የተናገራቸውን ሃሳቦች ዘርዝር፡፡ ሴትየዋ ኢየሱስ የሚሰጠውን ውሃ የፈለገችበት ምክንያት ምንድነው? አንተስ የኢየሱስን ስጦታ ለምድራዊ ነገርህን ለማሟያ ወይስ ዘላለማዊውን ማየት ችለሃል?
7. 20-24ትስ ትኩረት ያደረገበት አንድ ቃል ምንድነው? ቃሉ ስንት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል? የአምልኮ ሥፍራን አስመልክቶ በሴትየዋና በኢየሱስ መሃል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ተናገር፡፡ አንተስ ለአምልኮ ያለህ አመለካከት ምን ይመስላል?
8. ቁ25-26 ይህች ሴት ለኢየሱስ እውቀት እንዳላት የነገረቸው ስለ ምን ነበረ? ኢየሱስስ ሊገልጥላት የፈለገው እውነት ምን ነበረ? እንደዚህች ሴት ስለኢየሱስ እውቀት ያላቸው ነገር ግን ኢየሱስን በግል የማያውቁ ሰዎች ገጠመውህ ያውቃሉ ወይ? ስለ ኢየሱስ ማወቅ ብቻ በቂ ስላልሆነ ከኢየሱስ ጋራ በግል መተዋወቅህን እርግጠኛ ሁን፡፡

# <u>ጥናት ዘጠኝ ዮሐንስ 4፡27-42</u>

የጥናት ዓላማ፡- ወንገሉን ለሰዎች ተናግረን በእኛ ምስክርነት ለደህንነት አለመብቃታቸው ተስፋ ሊያስቆርጠን እንደማይገባና በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ተናግረን ሰዎች ማመናቸው የእኛ ሥራ ብቻ እንዳልሆነ ነገር ግን ከእኛ በፊት ብዙ ዘር የዘሩ ቅዱሳን ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብ እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ አንዱ ይዘራል፤ ሌላውም ያጭዳል የተባለው ምሳሌ እውነት ነው፡፡ ያልደከማችሁብትን እንድታጭዱ ላክኋችሁ፤ አድካሚውን ሥራ ሌሎች ሰሩ፤ እናንተም የድካማቸውን ፍሬ ሰበሰባችሁ፡፡›› ዮሐ 4፡37-38

1. ዮሐ 4፡27-42 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ27 ላይ ደቀመዛሙርቱን ያስደነቃቸው ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስን ለምን አነጋገርካት ብሎ ማንም አልጠየቀም ሲል፤ በተለይ ማን የማን ዝምታ ነው አንተን የሚያስገርምህ? ለምን?
2. ሴትየዋ ቁ28-30 መሰረት ያደረገችው ነገር ምን ነበረ? በዮሐ 1፡41 እና 45 ላይ እንድርያስና ፊሊጶስ ከመሰከሩት ምስክርነት የዚህች ሴት ምስክርነት የሚለይበት አንድ ነገር ምንድነው? ይህች ሴት እንስራውን እዚያው ትታ መሄዷ ምን ይነግረናል?
3. ቁ31-34 በደቀመዛሙርቱና በኢየሱስ መሃል የሚካሄደው ውይይት በምን ዙሪያ ያተኮረ ነው? ውይይታቸውን ስታደምጡ በሁለቱ መሃል መግባባት ያለ ይመስልሃል ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡ አ
4. ቁ34-35 ላይ ኢየሱስ ስለተልዕኮው የሚናገራቸውን ሁለት ነገሮች ተናገር፡፡ ኢየሱስ ይህንን ከምግብ ጋራ ያመሳሰለበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ለአንተስ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማድረግ የሚርብህና ዘወትር ለመፈጸም የምትሮጥለት ነገር ነው ወይ?
5. በቁ39 ላይና በቁ41 ላይ ደግሞ ‹‹ሌሎች›› በመባል የተጠቀሱት ሰዎች ያመኑበት መንገድ የሚለያየው እንዴት ነው? ከዚህ ሁኔታ ምን መማር እንችላለን?
6. በቁ 42 መሰረት ሰዎቹ በሴትየዋ ምስክርነት ወደ ጌታ ቢመጡም እንኳን የወሰዱት ሁለተኛው እርምጃ ምን ነበረ? ከእርሱ ከራሱ ከሰሙ በኋላ ስለ ኢየሱስ ማንነት በራሳቸው የደረሱበት እውነት ምን ነበረ? ከዚህ ምን ትምህርት ልንቀስም እንችላለን?
7. በቁ37-38 ላይ ኢየሱስ አድካሚውን ሥራ ሰሩ የሚላቸው እነማንን ነው? ለምን ይመስልሃል ደቀ መዛሙርቱ ይህንን እውነት እንዲረዱ ኢየሱስ የፈለገው? አንተስ ለሰዎች ወንጌልን ነግረህ በአንዴ ሲቀበሉ ሌሎች የደከሙበት እርሻ መሆኑን ምን ያህል ትገነዘባለህ? ስብከትህ ፍሬ ሳያፈራ ሲቀር ደግሞ እግዚአብሄር ሌላ የአዝመራ ሰብሳቢ አዘጋጅቶ ሊሆን ስለሚችል ተስፋ ሊያስቆርጥህ አይገባም፡፡

# ጥናት አስር ዮሐንስ 4፡43-54

የጥናት ዓላማ፡- ጌታ የተናገረውን ወይም የተስፋ ቃሉን አምነን የእምነት እርምጃ መራመድ በምንጀምርበት ጊዜ፤ በህይወታችን እንዲለወጡ እግዚአብሄርን የምንለምናቸው ነገሮች መልስ እንደሚያገኙ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ኢየሱስም ልጅህ በህይወት ይኖራልና ሂድ አለው፤ ሰውየውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አምኖ ሄደ፤ በመንገድ ላይ እንዳለም…ልጁ በህይወት መኖሩን ነገሩት፡፡›› ዮሐ 4፡50-51

1. ዮሐ 4፡43-54 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ የገሊላ ሰዎች ኢየሱስን የተቀበሉበት አቀባበል ምን ዓይነት ነበረ? የዚህ ዓይነት አቀባበል ያደረጉበት ምክንያት ለምን ነበረ?
2. በቁ46 ላይ የምናያቸው ሁለት ሰዎች እነማን ናቸው? ስለ ሹሙ ሰው የምናውቃቸውን ነገሮች ሁሉ ተናገር፡፡
3. ቁ47 ይህ ሰው ስለ ኢየሱስ ወደ ከተማቸው መምጣቱን ያወቀው በምንድነው? ወደ ኢየሱስ ቀርቦ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስ ይህንን ማድረግ የሚችል መሆኑን በምን ያወቀ ይመስልሃል? አንተስ ኢየሱስ ትናንት በህይወትህ ያደረገው ተአምራት ምን ያህል ለዛሬው እምነት ሆኖልሃል?
4. ይህ የቤተመንግስት ሹም ኢየሱስ ልጁን እንዲፈውስለት የጠየቀው በምን ዓይነት መንገድ ነው? ሹም ሆኖ እያለ በዚህ ዓይነት አቀራረብ ወደ ኢየሱስ መቅረቡ ምን የሚነግረን ነገር አለ ትላለህ? ኢየሱስ የመለሰለት መልስ ምን የሚል ነው?
5. በቁ49-50 ኢየሱስ ለተናገረው ንግግር የሰውየው ምላሽ ምን ነበረ? ለሁለተኛ ጊዜ ለለመነው ልመና የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበረ? አንተስ የመጀመሪያ ጸሎትህ ባይመለስ ተስፋ ቆርጠህ ታቆማህ ወይስ በእርሱ ፊት በትጋት ልመናህን ታቀርባለህ?
6. ከቅፍርናሆም እስከ ቃና ድረስ የ17 ማይል ርቀት ሲሆን ምናልባት ከሶስት እስከ አራት ሰዓት ሊወስድ እንደሚችል ይገምታሉ፡፡ በቁ52 ላይ ልጁ የተሻለበትን ሰዓት ሲናገሩ ‹‹ትናንት›› ብለው ነው ያሉት፡፡ ይህ ሰው ኢየሱስ የተናገረውን አምኖ ወደልጁ ሳይሄድ መቆየቱ ስለእምነቱ ምን የሚነግረን ነገር አለ?
7. ቁ50-51 ላይ ሰውየው አመነ ብሎ የሚነግረን ምኑን ነው? ይህ ሰው አምኖ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? እግዚአብሄር በቃሉ የተናገረውን አምነህ እርምጃ መውሰድ ተለማምደሃል ወይ? ካልሆነ ግን በልመና የሚጠፋው ጊዜ ምናልባትም የምሥጋና ጊዜ ሊሆን የሚገባው ይሆናልና የሰጠውን የተስፋ ቃል ይዘህ የእምነት እርምጃ መራመድ ጀምር፡፡

# ጥናት አስራ አንድ ዮሐንስ 5፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር በክርስቶስ ኢየሱስ ለነፍሳችን ፈውስን ሲያቀዳጀት፤ እርሱን አስከብረን በቅድስና እንድንኖር ስለሆነ፤ ተመልሰን በሃጥያት መመላለሳችን ለመለኮታዊ ቅጣት እንደሚያጋልጠን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ያንን ሰው በቤተ መቅደስ አግኝቶ እነሆ ተፈውሰሃል፣ ከእንግዲህ ግን ሃጥያት አትስራ፤ ያለበለዚያ ከዚህ የባሰ ይደርስብሃል አለው፡፡›› ዮሐ 5፡14

1. ዮሐ 5፡1-15 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ስለ መጠመቂያይቱ የተነገሩንን የተለያዩ ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡ በዚህች መጠመቂያ ቦታ ስለሰፈሩት የሰዎች ዓይነት ቁ3 ምን ይላል? በዚህ ስለሰፈሩት ሰዎች ቁጥርስ ምን የምናውቀው ነገር አለ?
2. እነዚህ ሁሉ ሰዎች እዚያ የሚገኙበትን ምክንያት በአንድ ቃል ተናገር ብትባል ምን ትላለህ? በቁ3 ላይ የምናነባቸው ሁለት ቃላት ‹‹እየተጠባበቁ›› ‹‹ይተኙ ነበር›› የሚሉት አብረው የማይሄዱ ይመስላሉ፡፡ እየተጠባበቁ መተኛት የሚለውን ሃሳብ እንዴት እንደሚገባህ አስረዳ፡፡
3. ውሃውን ያናውጥ ስለነበረው ሰው ማንነትና ስለሚያናውጥባቸው ጊዜያት የምታውቀውን ተናገር፡፡ በዚህ ሥፍራ ለመፈወስ መስፈርት ሆኖ የምናገኘው አንድ ነገር ምንድነው? ለነፍሳችን መዳን እግዚአብሄር መስፈርቱ በእውቀት፣ በሃብት፣ በአቋም ወይም በጉልበት በልጦ በተገኘ ቢሆን የአንተና የአንቺ ስፍራ የት ይሆን እንደነበረ አስብ፡፡ 1ኛ ቆሮ 1፡26ትን ማንበብ ይረዳል፡፡
4. ቁ5-9 ላይ የምናየው ኢየሱስ ያነጋግር የነበረውን ሰው ዮሐንስ ያስተዋወቀን ምን በማለት ነው? የኢየሱስ ጥያቄ ለዚህ ሰው ምን ነበረ? ለምንድነው ኢየሱስ የጠየቀው ጥያቄ ለብዙዎቻችን ስሜት የማይሰጥ አይነት ጥያቄ ሆኖ የሚገኘው?
5. በነዚሁ ቁጥሮች ላይ የህመምተኛው መልስ ምን ነበረ? ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ አግኝቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ፡፡ የሰውየው መልስ ይህ ሰው ለእርሱ ችግር ሆነው የሚያያቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
6. ሰውየው አጥጋቢ መልስ መስጠት አለመቻሉ ኢየሱስ እንዳይረዳው እንቅፋት ሆኖበት ታያለህ ወይ? በቁ8 ላይ ኢየሱስ ለዚህ ሰው የለኝም፣ ቀድሜም ለመግባት ችሎታ የለኝም ለሚል ሰው ምን ሲያደርግ እናያለን? በህይወትህ ሰው የለኝም ወይም አቅም፣ እውቀት፣ ትምህርትና… የመሳሰሉት ነገሮች የሉኝም የሚል አመለካከት ካለህ ኢየሱስ ለአንተም/ለአንቺም እንደሚቆም ልታዩ ይገባል፡፡
7. በቁ14 ኢየሱስ ለፈወሰው ሰው የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበረ? የነፍስህን ፈውስ ለተቀበልነው ለእኛ ይህ ማስጠንቀቂያ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል አስረዳ፡፡ አንዴ ለነፍሴ ፈውስን ተቀብያለሁ ብሎ በሃጥያት ዙሪያ ለመኖር መሞከር፤ ራስን ለመለኮታዊ ቅጣት ማጋለጥ ስለሆነ በቅድስና መመላለስን እለት እለት ተለማመድ፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት ዮሐንስ 5፡16-30

የጥናት ዓላማ፡- ዛሬ ህይወት እንዲሆንላቸው የኢየሱስን ድምጽ መስማት ያልፈለጉ ሁሉ፤ አንድ ቀን ሳይወዱ ለፍርድ የሆነውን ድምጹን የሚሰሙበት አስፈሪ ቀን እንደሚመጣ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በዚህ አትደነቁ፤ መቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤ መልካም የሰሩ ለህይወት ትንሳኤ፣ ክፉ የሰሩ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉ፡፡›› ዮሐ 5፡28-29

1. ዮሐ 5፡16-30 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ16-18 ላይ ኢየሱስን የጠሉትና ያሳደዱት በምን ምክንያት ነበረ? ለዚህ ስደት የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበረ? አንተንስ ሰዎች ቢጠሉና ቢያሳድዱህ እንደ ኢየሱስ መልካም በማድረግህ ወይስ በሰዎች ላይ ክፉ በማድረግህ ነው የምትጠላው?
2. በቁ18 ላይ ስንመለከት በአይሁድ አመለካከት ኢየሱስን ለሞት እንደሚያበቃው ያነሷቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን ነበሩ? ከዚህ የተከተሉትን ጥቅሶች ስታይ ኢየሱስ ፈርቶ ሃሳቡን ቀየረ ወይስ ይበልጥ የጀመረውን ሃሳብ አጠናከረ ትላለህ? አስረዳ፡፡
3. ቁ19-23 በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ላይ በተደጋጋሚ የተጠቀሱት ሁለት ቃላት ምንና ምንድናቸው? እያንዳንዳቸው ስንት ስንት ጊዜ እንደሰፈሩ ተናገር፡፡
4. በነዚህ ቁጥሮች ላይ የአብና የወልድን ግንኙነት አንድ ቃል በመጠቀም ግለጽ ብትባል ምን ትላለህ? ቁ21-23 ትኩረት የተደረገባቸው ሶስት ርዕሶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ከሙታ ማስነሳት የማን ሃላፊነት ሆኖ ነው የተነገረው?
5. በቁ23-24 የፍርድን ሃላፊነት የተቀበለው ከስላሴዎች መሃል ማን ነው? በነዚሁ ቁጥሮች ላይ ሰዎች ሁሉ ክብር እንዲሰጡት የሚገባው ማን ነው? አብና የወልድ እኩል እንደሆኑ በቁ18 እየነገረን በስራ ድርሻ ደግሞ ክፍፍል መኖሩ ምን ሊያስተምረን የሚችለው ነገር እንዳለ ተወያዩበት፡፡
6. ሰው የዘለዓለም ህይወት ሊኖረው እንዲችል ሁለቱ ማድረግ የሚኖርበት ነገሮች በቁ24 መሰረት ምንና ምንድናቸው? የዚህ ዓይነቱ ሰው በማመኑ ካገኛቸው ብዙ ነገሮች ውስጥ በዚህ ስፍራ የተጠቀሱትን ተናገር፡፡ ‹‹ቃሌን የሚሰማ›› ሲል ኢየሱስ ሲናገር የሰሙት ሰዎች ሁሉ የዘለዓለም ህይወት አላቸው ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነ ግን ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ፡፡
7. በቁ28-29 መሰረት የኢየሱስን ድምጽ የሚሰሙት ሰዎች እነማንናቸው? ይህ ክፍል እነዚህን ሰዎች በስንት ይከፍላቸዋል?
8. በቁ24 ላይ ባሉት ሰሚዎችና በ28 ላይ ባሉት ሰሚዎች መሃል ያለው ትልቁ ልዩነት ምንድነው ትላለህ? አንተስ ዛሬ ብርሃን ሳለና ኢየሱስ በቃሉ ለዘለዓለም ህይወት ሲጠራህ ሰምተኸዋል ወይ? ዛሬ እድሉ እያለህ ድምጹን ለመስማት ጆሮህን ብትነፍገውና እንቢ ብትል፤ ሳትወድ በግዴታ ድምጹን ለፍርድ የምትሰማበት ቀን እንደሚመጣ እወቅ፡፡

# ጥናት አስራ ሶስት ዮሐንስ 5፡31-47

የጥናት ዓላማ፡- መጽሃፍ ቅዱስን መማራችን፣ መመርመራችንና ማጥናታችን ሁሉ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን፤ ሆኖም ህይወት በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ እንጂ በመጻህፍት ውስጥ ስላልሆነ ህይወት እንዲሆንልን ወደ እርሱ መምጣት አማራጭ የሌለው ነገር መሆኑን አስረግጠን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በእነርሱ የዘላለም ህይወትን የምታገኙ እየመሰላችሁ፣ መጻህፍትን ትመረምራላችሁ… እናንተ ግን ህይወት እንዲኖራችሁ ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም፡፡›› ዮሐ 5፡39-40

1. ዮሐ 5፡31-47 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ31-37 ላይ በተደጋጋሚ የሰፈረው አንድ ቃል ምንድነው? ይህንን ቃል በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንት ጊዜ እናገኘዋለን?
2. በቁ31 ላይ ኢየሱስ ‹‹ምስክርነቴ ተቀባይነት አይኖረውም›› ሲል ምስክርነቴ ልክ አይደለም ወይም ውሸት ነው ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ምን ማለቱ ነው? ከዚህ አነጋገሩ ለራሳችን ትምህርት ሊሆነን የሚችል ምን እውነት ታያለህ?
3. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት ኢየሱስ ስንት ምስክሮች እንዳሉት እናያለን? ማን ማን እንደሆኑና የት እንደሚገኙ ጥቅሱን ተናገር፡፡ ማቴ 18፡16 ስለምስክር ምን ይነግረናል?
4. እነዚህን ሁሉ ምስክሮች ሁሉ መጥራቱና የእርሱን ከአብ መላኩን ለማረጋገጥ ይህንን ሁሉ መናገር ስላስፈለገበት ምክንያት ቁ34 ምን ይናገራል? እነዚህ ሰዎች በቁ18 ላይ እግዚአብሄር አብን እንደሚያውቁ ይናገራሉ፡፡ ኢየሱስ በቁ37 እና 41 ላይ ስለራሳቸው የሚነግራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
5. በቁ43-44 ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች የሚወቅስባቸው ሁለት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ እንደዚህ ማድረጋቸው ያስቀረባቸው ትልቅ በረከት ምንድነው ይላል ኢየሱስ? አንተስ ክብርን የምትፈልገው ከአንዱ ከእግዚአብሄር ወይስ ሟች ከሆነው ሰው?
6. ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች ለመዳናቸው ተስፋ የጣሉት በማን ላይ ነው ይላል በቁ45-47? ይህ የታመኑበት ሰው ከማዳን ይልቅ ምን እንደሚያደርግ ነው የሚነግራቸው? አንተስ ከኢየሱስ ሌላ የምትታመንበት ሌላ ሰው አለህ ወይ? ለፍርድ ቀን የሚያዋጣህ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን እወቅ፡፡
7. ሙሴ የጻፈውን ነገር ከኢየሱስ ለይቶ ማየት የማይቻለው ለምንድነው? በኢየሱስ አነጋገር ሙሴ የጻፈውን አምነው ቢሆን፤ የሚከተለው ነገር ምን ይሆን ነበር ማለት ነው?
8. ቁ39 ላይ ተመልሰን ስናነብ በእነዚህ ሰዎች አመለካከት የዘላለም ህይወት የሚገኘው ምን በማድረግ ነው? ኢየሱስ የዘላለም ህይወት የሚገኝበት ትክክለኛው መንገድ ምንድነው ይላቸዋል? አንተስ ህይወት የሚገኘው ብዙ የሃይማኖት መጻህፍት በመመርመር ሳይሆን ህይወት ወደሆነው ወደ ኢየሱስ በመምጣት ብቻ መሆኑን ተረድተሃል ወይ?

# ጥናት አስራ አራት ዮሐንስ 6፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- ችግር በህይወታችን ሲገጥመን ከችግሩ ልንወጣ የምንሞክረው አንዳንዴ እንደሌላ ገፋ ማድረግ፣ ሌላ ጊዜ ምናልባት በገንዘብና በዘመድ፣ አንዳንዴ ደግሞ ግራ በመጋባት የተለያዩ ነገሮች መሞከር ይሆናል፤ ነገር ግን ለማንኛውም ነገር ትክክለኛ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ጌታ መሆኑን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ኢየሱስም ሰዎቹ እንዲቀመጡ አድርጉ አለ፡፡ በዚያ ቦታ ብዙ ሳር ነበረ፤ አምስት ሺህ ያህል ወንዶች ተቀመጡ፤ ኢየሱስ አምስቱን እንጀራ አንስቶ አመሰገነ ለተቀመጡት ሚፈልጉትን ያህል አደለ አሳውንም እንዲሁ፡፡›› ዮሐ 6፡10-11

1. ዮሐ 6፡1-15 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ የምታያቸውን ሰዎች በሙሉ ዘርዘር፡፡ ይህንን የሚያህል ህዝብ ወደ ኢየሱስ የመጣው በምን ምክንያት ነው?
2. ኢየሱስ በቁ5-7 ለፊሊጶስ ያቀረበው ጥያቄ ምን ነበረ? ኢየሱስ ለሚከተሉት ሰዎች ለሥጋቸው ስለሚያስፈልጋቸው ነገር መቆርቆሩ፤ የእርሱ ተከታዮች ለሆነው ለእኛ መልካም ዜና ሆኖ የምታየው በምን መንገድ ነው?
3. ኢየሱስ በዚህ ክፍል መሰረት ጥያቄውን ያቀረበበት ምክንያት ምን ነበረ? ፊሊጶስ የኢየሱስን ፈተና አልፏል ትላለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
4. እንድርያስ በቁ8 ላይ ከተናገረው አነጋገር ስለ እምነቱ መረዳት የምንችለው ምን ነገር አለ? በአንተ አስተያየት በፊሊጶስና በእንድርያስ እምነት መካከል የምታየውን ልዩነት አስረዳ፡፡
5. ማቴ 14፡13-21 ላይ ደቀመዛሙርቱ ስለህዝቡ ለኢየሱስ የሰጡት ምክር ምን ነበረ? እርሱ የመለሰላቸው ምን በማለት ነው? በማቴ 14፡13 ስናይ ኢየሱስ ያደረገውን ለማድረግ የገፋው ነገር ምንድነው ትላለህ? አንተስ ለሰዎች የምታደርገውን ነገር እንድታደርግ የሚገፋህ ነገር ምንድነው?
6. ዮሐ 6፡12-15ትን ስታነብ ኢየሱስ ያደረገው ተአምራት በበሉት ህዝብ ውስጥ ያስከተለው የአመለካከት ለውጥ ምን ነበረ? ከዚህ አመለካከታቸው ተነስተው ማድረግ የፈለጉት ነገርስ ምንድነው? በአመለካከታቸውና ሊያደርጉ ባሰቡት ነገር መሃል የምታየውን ቅራኔ ለወገኖች አካፍል፡፡
7. በዚያ ስፍራ ኢየሱስ የመገባቸው ሰዎች ቁጥር በግምት ምን ያህል ነበረ ትላለህ? ሉቃ 9፡14ትን ስናነብ ህዝቡን በምን ዓይነት አቀማመጥ እንዲያስቀምጡ ነው ለደቀመዛሙርቱ መመሪያ የሰጠው? በዚህ ተአምር ዙሪያ ደቀመዛሙርቱ የነበራቸው ድርሻ ምን ነበረ?
8. ለሰዎቹ ረሃብ በዚህ ክፍል የቀረቡት አራት መፍትሄዎች ምን ምን እንደነበሩ ተናገር፡፡ ከእነዚህ በየትኛው ምድብ ውስጥ ራስህን ታየዋለህ? ምንጊዜም ለችግራችን ትክክለኛው መፍትሄን ለማግኘት ወደየሱስ መቅረብ አማራጭ የለውም፡፡

# ጥናት አስራ አምስት ዮሐንስ 6፡16-29

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ እንድናገለግለውና የእርሱን ሥራ እንድንሰራ መፈለጉ የታወቀ ቢሆንም እንኳን፤ በቅድሚያ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን የመጀመሪያው ሥራችን እንድናደርገው እንደሚፈልግ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እነርሱም ታዲያ የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት ምን ማድረግ አለብን አሉት፡፡ ኢየሱስም እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ ይህ የእግዚአብሄር ስራ ነው ሲል መለሰላቸው፡፡›› ዮሐ 6፡28-29

1. ዮሐ 6፡16-29 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቀ16-19 ላይ ደቀመዛሙርቱ ለብቻቸው የነበሩበት ምክንያት ለምን ነበረ? በጀልባ ወደ ቅፍርናሆም ለመሻገር ሲነሱ አጠቃላይ ሁኔታው ምን ይመስል እንደነበረ አስረዳ፡፡
2. ደቀመዛሙርቱን ያስደነገጣቸው ነገር ምን ነበረ? በቁ20 ከኢየሱስ አነጋገርና በማቴ 14፡26-27 ላይ ከምናነበው፤ ደቀመዛሙርቱ የመሰላቸው ምን ነበረ?
3. ቁ22-25 ጌታ አምስት ሺህ ሰዎችን በመገበበት ማግሥት የዛሬው ምንባብ የሚነግረንን በራስህ አማርኛ ለወገኖች ተናገር፡፡ ኢየሱስን የፈለጉት ሰዎች ባገኙት ጊዜ ጥያቄአቸው ምን የሚል ነበረ?
4. በቁ26-27 ላይ የምናያቸው ሰዎች ኢየሱስን እየተከተሉ ያሉት ምን ፈልገው ነው? ለነዚህ ሰዎች የኢየሱስ ምክር ምን የሚል ነው? አንተስ ለመሆኑ ኢየሱስን ለምን እንደምትከተለው በጥልቀት አስበህ ታውቃለህ ወይ?
5. እነዚህ ኢየሱስን እየተከተሉት ያሉት ሰዎች በቁ28-29 ላይ ለኢየሱስ የነበራቸው ጥያቄ ምን ነበረ? ለጠየቁት ጥያቄ ኢየሱስ ምን መለሰላቸው?
6. ማህተም በእኛ ዘመን እንዴትና ለምን እንደምንጠቀምበት ተወያዩበት፡፡ ማህተምን አስመልክቶ ከተወያያችሁበት አንጻር በቁ27 ላይ ‹‹ለዚህም እግዚአብሄር አብ ማረጋገጫ ማህተሙን በእርሱ ላይ አትሟልና›› ሲል እንዴት ምን ማለቱ እንደሆነ ተናገር፡፡
7. ቁ26-27 እና በቁ28-29 ኢየሱስ በሁለቱም ሥፍራዎች የተናገረውን በመመልከት፤ እነዚህ ሰዎች ነገሮችን የሚያዩት አገላብጠው ነው ማለት የምንችልበትን ምክንያት ምነ እንደሆነ አስረዳ፡፡ አንተስ የምድራዊውንና የሰማያዊውን ትክክለኛ ቅደም ተከተል ምን ያህል ተረድተኸዋል? የሚቀድመው እግዚአብሄርን ማገልገል ሳይሆን እርሱ በላከው ማመን ሲሆን፤ አገልግሎቱ ከዚያ የሚከተል ነው፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት ዮሐንስ 6፡30-51

የጥናት ዓላማ፡- የእስራኤል ልጆች ሰማያዊ እንጀራን በሙሴ በኩል መቀበላቸው ሙሴን የተአምራቱ ባለቤት እንደማያደርገው ሁሉ፤ በእኛም ህይወት ፈውስ ወይም ልዩ በረከት በወገኖች በኩል ስናገኝ የክብሩ ባለቤት እግዚአብሄር ራሱ መሆኑን እንዳንዘነጋ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ እውነተኛን እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው፡፡›› ዮሐ 6፡32

1. ዮሐ 6፡30-51 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ30 ላይ ‹‹አይተን እንድናምን›› የሚለው አነጋገር በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ማንን ያስታውስሃል? እነዚህ ሰዎች ተአምር ቢያዩ በኢየሱስ ለማመን የተዘጋጀ ልብ አላቸው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
2. በቁ31-35 ላይ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የምናየው አንድ ቃል ምንድነው? ይህ ቃል ስንት ጊዜ ተጠቅሷል? ይህ ቃል በዚህ ምንባብ መሰረት በአብዛኛው የሚጠቁመው ወደማን ነው?
3. በቁ33 ውስጥ ስለዚህ እንጀራ ማየት የምንችላቸውን ቢያንስ ሶስት እውነቶች ተናገር፡፡ ቁ34 ላይ ‹‹ይህንን እንጀራ ሁልጊዜ ስጠን›› ሲሉ በቁ33 ላይ የተነገረውን በመረዳት ይመስልሃል ወይ? ለምን?
4. በቁ35-40 አነጋገር ሰማያዊውን እንጀራ መብላት ማለት ምን ማለት ነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ  ኢየሱስ ከተናገረው ነገር አማኞችን በደህንነታቸው ተረጋግተው ሳይፈሩ እንዲመላለሱ ይረዷቸዋል የምትላቸውን ሃሳቦች በሙሉ ዘርዝር፡፡
5. በቁ41-42 ላይ ከኢየሱስ አነጋገር ለአይሁድ እንቅፋት የሆነባቸውና ሊዋጥላቸው ያልቻለው ምን የሚለው ሃሳብ ነበረ? ለምንድነው ይህ ሃሳብ ለእነዚህ ሰዎች አስቸጋሪ የሆነባቸው?
6. ኢየሱስ በቁ43-44 ላይ ከተናገረው ንግግር መማር የምንችለው አንድ የክርስትና እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
7. በቁ48-51 ላይ በብዛት የሚታየው አንድ ቃል ምንድነው? በአንተ አመለካከት የዛሬውን ምንባብ በአጠቃላይ ስንመለከት በብዛት ኢየሱስ ትኩረት ሰጥቶ የተናገረበት አንድ ቃል ምንድነው ትላለህ? አይሁድ የተሰናከሉበትና ኢየሱስ መልሶ የተጠቀመበት ሃሳብ ምንድነው? በአንተ አመለካከት ኢየሱስ ሰዎች የተሰናከሉበትን ይህንን ሃሳብ ለምን መጠቀም ለምን የቀጠለ ይመስልሃል?
8. እንጀራን አስመልክቶ በቁ32 ላይ ስንመለከት እነዚህ ሰዎች ከሰማይ መናን የሰጣቸው ማን እንደሆነ ነው የሚያስቡት? ኢየሱስ እንጀራው ከማን እንደተሰጣቸው እንዲያውቁ ነው የሚናገራቸው? አንተስ  በረከትህ በወንድም እገሌ ጸሎት፣ ትንቢት፣ መገለጥና ፈውስ በማለት ሰጪውን የረሳህበት ጊዜ ይኖር ይሆን? ያዕ 1፡17 እንደሚናገረው መልካም ስጦታ ሁሉ ከላይ ስለሆነ ክብር ሁሉ ለእርሱ ይገባል፡፡

<u>ጥናት አስራ ሰባት ዮሐንስ 6፡52-71</u>

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ እውነትን በግልጽ መናገር እንጂ ቁጥር ለማብዛት ትምህርቱን እንዳልበረዘ ሁሉ፤ እኛም በቁጥር መጨመር ላይ በማተኮር ማዕከላዊ መልዕክታችንን ማመቻመች እንደማይኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከዚያም በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ብዙዎች ወደኋላ ተመለሱ፤ ከዚያ ወዲያ አልተከተሉትም፤ ኢየሱስም አስራ ሁለቱን፣ እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ አላቸው፡፡›› ዮሐ 6፡66-67

1. ዮሐ 6 52-71 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ52-54 ውስጥ አይሁድን ያከራከር የነበረው ነገር ምንድነው? የከርክራቸውስ መሰረት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ቁ53ትና ቁ35 ለሚያነብ ሰው የሰውን ልጅ ሥጋ መብላት ለሚለው ምን ትርጉም ያገኛል ትላለህ?
2. ቁ58-59 አባቶቻቸው የበሉት እንጀራ ኢየሱስ ከሚሰጠው እንጀራ የሚለይባቸውን ሁለት መንገዶች ተናገር፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ትምህርቶቹን ያስተማረበት ሥፍራ የት ነበረ? አንተስ ኢየሱስ የሚሰጠውን እንጀራ በልቻለሁ ብለህ ታምናለህ ወይ?
3. የኢየሱስ ትምህርት ከብዶ የተገኘው ለምን ያህል ሰዎች ነበረ? ከትምህርቱ መሃል ለሰዎቹ የከበዳቸው ምን የሚለው ሃሳብ ነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ከቃሉ ለመቀበል የሚከብድ ነገር ሲገጥምህ የምትወስደው እርምጃ ምንድነው?
4. ቁ61-63ትን ስንመለከት ኢየሱስ ትምህርቱ ለሰዎቹ እንደከበደና ማጉረምረም እንደያዙ የነገረው ማንነው? ማጉረምረማቸውን አስመልክቶ ኢየሱስ በዚህ ክፍል ምን ሲናገር እንመለከታለን?
5. በዚህ ዓውደ ምንባብ አማካኝነት ስናየው ‹‹እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስም ህይወትም ነው›› ሲል በአንተ አመለካከት ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ፡፡
6. በቁ64-65 መሰረት ኢየሱስ ወደኋላ ለማለት የተዘጋጁት ሰዎች ቀድሞም ቢሆን በእርሱ እንዳላመኑ የተረዳው መቼ ነበረ? ቁ65ትን ከቁ44 ጋራ በማገናዘብ ደህንነትን አስመልክቶ አንድ የምንማረው እውነት ምንድነው?
7. በቁ60-61 ላይ ትምህርቱ ስለከበዳቸውና ስላጉረመረሙት ሰዎች መጨረሻ ቁ66 ምን ይናገራል፡፡ ከኢየሱስ እውቀት በመነሳት ቁ64 ስለእነዚህ ሰዎች እምነት በድፍረት መናገር የምትችለው እውነት ምንድነው? ይህንን ሃሳብ በመመርኮዝ፤ አንዳንድ ሰዎች ጌታን መከተል ሲያቆሙ ቀድሞም አላመኑም ወይም አልዳኑም ማለት የማንችለው ለምንድነው?
8. በቁ67-71 ስንመለከት ያለ ኢየሱስ መኖር እንደማይቻል የተረዳ ሰው ማን ነው? ይህ ሰው የተናገረው ስለራሱ ብቻ ነው ወይስ የሚወክላቸው ሰዎች አሉ? ይህንን ሲል ምክንያቱ ምን ነበረ?
9. ጴጥሮስ መልሱን የሰጠው ምን ለሚለው ጥያቄ ነበረ? የተከተሉት ሁሉ ትተውት ሄደው ትምህርቱን ሳይቀይር አስራ ሁለቱ ደግሞ የመሄድ ምርጫ እንዳላቸው መናገሩ ምን ያስተምረናል? አንዳንድ ለሰዎች የሚከብድ እውነት የሚያሸሻቸው ሰዎች ካሉ መፍትሄው ትምህርቱን ቀይሮ እነሱን ማቆየት ሳይሆን ለእግዚአብሄር እውነት ታማኝ ሆኖ መገኘት እንደሆነ ለመማር፡፡

# ጥናት አስራ ስምንት ዮሐንስ 7፡1-24

የጥናት ዓላማ፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ላይ ሊሰነዘር ያለውን ክፉ ነገር ሁሉ ማስቀም እየቻለ በጥበብ መራመድ ካስፈለገው፤ እኛም እግዚአብሄር ያድነኛል በሚል ወደማያስፈልግ መከራ ውስጥ ራሳችንን ማስገባት መንፈሳዊነት ሳይሆን እግዚአብሄርን መፈታተን እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በይሁዳ አውራጃ መዘዋወር ትቶ በገሊላ ተዘዋወረ…ይሁን እንጂ ወንድሞቹ ወደ በዓሉ ከሄዱ በኋላ እርሱም በግልጥ ሳይሆን በስውር ወደ በዓሉ ሄደ፡፡›› ዮሐ 7፡1 እና 7፡10

1. ዮሐ 7፡1-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ ለምን ነበረ በቁ1 ላይ ኢየሱስ ያስተምርበት የነበረውን መቀየር ያስፈለገው? በዚህ ሁኔታ ውስጥ ወንድሞቹ ይገፋፉት የነበረው ወዴት እንዲሄድ ነበረ?
2. ወንድሞቹ በ3-4 ላይ ኢየሱስን ወደ ይሁዳ እንዲሄድ ሲናገሩት የሰጡት ምክንያቶች ምን ነበሩ? ወንድሞቹ ካቀረቡት ሃሳብ ሌላ ዮሐንስ ስለ እነርሱ የተናገረው አንድ እውነት ምንድነው?
3. በቁ6-9 ውስጥ ኢየሱስ እያነጻጸረ የሚናገረው ማንንና ማንን ነው? ጊዜን አስመልክቶ ኢየሱስና ወንድሞቹ ያላቸው የአመለካከት ልዩነት ምን እንደሚመስል አስረዳ፡፡
4. በዚሁ ቁ6-9 ባለው ቁጥር ውስጥ ስለ ጊዜ እየተናገረ የዓለምን ጥላቻ ማስገባት የስፈለገው በምን ምክንያት ነው ብለህ ትገምታለህ?
5. ከምንባቡ ስንመለከት ኢየሱስ ወደ በዓሉ የሄደው መቼ ነበረ? ቁ10 ስለሄደበት ሁኔታ የሚናገረው ተጨማሪ እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
6. በበዓሉ ላይ በተገኙት ሰዎች መሃል ይካሄድ ስለነበረው ሁኔታ ቁ11-13 የሚነግረን አንድ እውነት ምንድነው? በነዚሁ ሰዎች መሃል ስለ ኢየሱስ ማንነት የተነገሩት ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
7. ቁ14-19ን በማንበብ፤ በዚህ ምንባብ ውስጥ አይሁድን ያስገረመው ነገር ምን ነበረ? እያስተማራቸው ያለውን ትምህርት አስመልክቶ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ የተናገራቸውን እውነቶች ሁሉ በራስህ ቋንቋ ተናገር፡፡
8. በቁ20-24 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እነዚህ ሰዎች ትምህርቱን ከመቃወም አልፈው ስለ ደረሱበት ሁኔታ ምን እናያለን? እነዚህን ሰዎች ስላስቆጣውና እዚህ ደረጃ ስላደረሳቸው ምክንያት ኢየሱስ ምን ይናገራል?
9. መለስ ብለን ስንመለከት በቁ1 ሊገድሉት ስለሚፈልጉ የሚያገለግልበትን መንደር መቀየሩ፤ በቁ10 ደግሞ በዚሁ ምክንያት በግልጥ ሳይሆን በስውር ለመሄድ መወሰኑ ምን ያስረዳናል? ከኢየሱስ አድራጎት ምን መማር እንችላለን? ወደማያስፈልግ መከራ ውስጥ ራስን ማስገባት መንፈሳዊነት ስላልሆነ የእግዚአብሄርን ፈቃድ አውቀህ በጥበብ መመላለስ ሃላፊነትህ መሆኑን አትዘንጋ፡፡

# ጥናት አስራ ዘጠኝ ዮሐንስ 7፡25-36

የጥናት ዓላማ፡- እነዚህ ሰዎች ክርስቶስ ከየት እንደሆነ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኞች ሆነው እንደተሳሳቱ፤ እኛም እርግጠኞች በሆንባቸው ነገሮች እንኳን ሰዎች ስለሆንን ልንስት እንደምንችል መዘንጋት እንደሌለብን ለመማር፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ይህ ሰው ከየት እንደሆነ እኛ እናውቃለን፤ ክርስቶስ ሲመጣ እኮ ከየት እንደሆነ ማንም አያውቅም፡፡›› ዮሐ 7፡27

1. ዮሐ 7፡25-36 በአንድነት ይነበብ፡፡ ክርስቶስ በአደባባይ እንደልቡ ማስተማሩ በህዝቡ አዕምሮ ውስጥ የፈጠረው ጥያቄ ምን ነበረ? የተሰበሰበው ህዝብ ራሳቸው ጠይቀውት ለነበረው ጥያቄ ራሳቸው የሰጡት ማብራሪያ ወይም መልስ ምን የሚል ነው?
2. በቁ25-29 ውስጥ በተለያየ መንገድ ተደጋግሞ የተነገረ አንድ ቃል ምንድነው? ይህስ ቃል በአብዛኛው የተጠቀሰው ከማን ጋራ በተያያዘ ነው?
3. በቁ30-31 ‹‹ጊዜው ገና ስላልደረሰ›› የሚለው አነጋገር ስለየትኛው ጊዜ የሚናገር ሃሳብ ነው? በነዚህ ቁጥሮች ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረው ትምህርት ላይ ያገኛቸው ሁለት ዓይነት ምላሾች ተናገር፡፡ አንተስ ለክርስቶስ ወንጌል የሰጠኸው ምላሽ የትኞቹን ይመስላል?
4. ቁ32 ላይ ፈሪሳውያኑ ከህዝቡ ሰሙ የሚለን ጉምጉምታ ምን ነበረ? በዚህ ክፍል የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያኑ ኢየሱስ እንዲያዝ የወሰኑት ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
5. ‹‹ከእናንተ ጋራ የምቆየው ጥቂት ጊዜ ነው›› ቁ33 ሲል ቆይታው እስከመቼ ነው ብለህ ታምናለህ? በቁ34 አነጋገር ኢየሱስ በሞት ተይዞ በመቃብር እንደማይቀር የሚያረጋግጥልን የትኛው ሃሳብ ነው? አንተስ ራስህ መቃብር ቋሚ ቤትህ እንዳልሆነና ወዳባትህ እንደምትሄድ ምን ያህል እርግጠኛ ነህ?
6. ቁ35-36 ላይ ለአይሁድ አዕምሮ ጥያቄ የሆነባቸው ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስ የሚናገረውና አይሁዶቹ ያሰቡት ነገር ተቀራራቢነት አለው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይመስልሃል አብዛኛውን ጊዜ አይሁድና ኢየሱስ በአመለካከት በጣም ሲራራቁ የሚታየው?
7. በቁ27 ላይ ተመልሰን ሰዎቹ የሰነዘሯቸውን ሁለት አረፍተ ነገሮች ምንና ምን የሚሉ ናቸው? እነዚህ ያሏቸው ነገሮች ትክክል ናቸው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን? ቁ49 ፈሪሳውያኑ ስለህዝቡ እውቀት ምን ይላሉ? አንተስ የማታውቀው ብዙ መንፈሳዊ እውነት እንዳለ ምን ያህል ትቀበላለህ? በእርግጠኛነት የያዝከው እውነት ምናልባትም ስህተት ሊሆን ስለሚችል ለመታረምና እውነቱን ለመቀበል የተከፈተ አዕምሮን መያዝ ብልህነት ነው፡፡

# ጥናት ሃያ ዮሐንስ 7፡37-53

የጥናት ዓላማ፡- ኒቆዲሞስ በብዙ ተቃዋሚዎች መሃል ለብቻው ለእውነት ለመቆም ቆራጠኛነትን እንዳሳየ እኛም ራሳችንን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ስናገኝ የሚያስከፍለንም እንኳን ቢሆን ለእውነት መቆም ክርስትያናዊ ግዴታችን እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ህጋችን አስቀድሞ አንድን ሰው ሳይሰማና ምን እንዳደረገ ሳይረዳ ይፈርድበታልን? እነርሱም፣ አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነብይ ከገሊላ እንደማይነሳ መርምር ትደርስበታለህ›› ዮሐ 7፡51-52

1. ዮሐ 7፡37-53 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ37 ላይ የሚናገረው ስለየትኛው በዓል ነው? ዘሌ 23፡33-34ትን በማንበብ ኢየሱስ ይህንን የተናገረው በበዓሉ በስንተኛው ቀን ነው ትላለህ? ይህንን ቀን ዮሐንስ ምን በማለት ነው የሚጠራው?
2. ኢየሱስ በዚሁ ቁጥር ላይ ጥሪ ሲያስተላልፍ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ጥሪ ውስጥ ኢየሱስ የሚሰጠውን ውሃ አስመልክቶ የተነገሩትን ቢያንስ አምስት ነገሮችን ዘርዝር፡፡
3. ቁ38-39 ትን በማንበብ ኢየሱስ ውሃ በማለት ከላይ በቁ37 ላይ የተናገረው ስለምን ነበረ? ‹‹የህይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል›› ሲል ምን ለማለት እንደፈለገ ነው የምትረዳው? ይህ የህይወት ውሃ ምንጭ ከውስ የመፍለቅ ነገር በአንተ ህይወት ይህ ተፈጻሚ ሆኗል ትላለህ ወይ?
4. የኢየሱስ የህይወት ውሃ የመስጠት ጥሪ በሰሚዎቹ መሃል ያስከተለው ነገር ምን ነበረ? በቁ40-43 ባለው ውስጥ ስለኢየሱስ ማንነት ስንት ዓይነት አመለካከቶችን እናያለን? አንተስ ስለኢየሱስ ማንነት ብትጠየቅ ማነው ትላለህ?
5. የቤተመቅደስ ጠባቂዎቹ በቁ32 ላይ የተሰጣቸው ተልዕኮ ምን ነበረ? ጠባቂዎቹ ኢየሱስን ይዘው ወደ ፈሪሳውያን ያላመጡበት ለምንድነው? ? በፈሪሳውያኑ ዓይን ጠባቂዎቹ እንዴት ነው የታዩት?
6. ቁ48-49ኝ ላይ ፈሪሳውያኑ የተናገሩት የንቀት አነጋገር፤ በማቴ 11፡25 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከጸለየው ጸሎት ጋራ የሚያያዘው በምን መንገድ ነው? አንተስ እንደ ፈሪሳውያኑ እግዚአብሄር ያከበራቸውን በንቀት የምትመለከትበት ጊዜ አለ ወይ?
7. ኒቆዲሞስ ማን ነበረ? በቁ51 ላይ ከምናነበው አነጋገሩ አንድ ሰው ላይ ለመፍረድ መመዘን ያለባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በነዚህ ነገሮች ሲመዘን የኢየሱስ ትምህርቱና ሥራው ማለትም ተአምራቶቹ የሚያስፈርዱበት ናቸው ወይ?
8. የኒቆዲሞስ ጥያቄ በራሱ ላይ ያስከተለበት ነገር ምን ታያለህ? እነርሱ ብዙዎች ሲሆኑ ብቻውን ለእውነት ለመቆም መወሰኑ ምን ያስተምርሃል? ለብቻ እውነትን ይዞ መቆም በጣም ከባድ ነገር እንደሆነ ቢታወቅም፤ አንተም እንደ ኒቆዲሞስ ውርደትና ስድብ ቢያስከትልብህም ለእውነት የመቆም ሃላፊነት እንዳለብህ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሃያ አንድ ዮሐንስ 8፡1-11

የጥናት ዓላማ፡- ከኢየሱስ የሃጥያት ይቅርታን የተቀበልን ሁላችን መወገርና መሞት የሚገባን እንደነበርን እንድንገነዘብና ምህረቱ ከሃጥያት እንድንለይ ከሚል ትዕዛዝ ጋራ መምጣቱን እንዳንረሳ ለማሳሰብ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አንቺ ሴት ሰዎቹ የት ሄዱ የፈረደብሽ የለምን? አላት እርሷም ጌታ ሆይ አንድም የለም አለች፡፡ ኢየሱስም እኔም አልፈርድብሽም በይ ሂጂ ከእንግዲህ ግን ሃጥያት አትስሪ አላት፡፡ዮሐ 8፡10-11

1. ዮሐ 8፡1-11 በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ የምታያቸውን ሰዎች ሁሉ ዘርዝር፡፡ በዚህ ስፍራ የተካሄደውን ነገር ሁለት ሰዎች በራሳቸው አነጋገር ታሪኩን በአጭሩ ይናገሩ፡፡
2. በቁ1—3ትን ስንመለከት ህዝቡ፣ ኢየሱስ፣ እና ፈሪሳውያኑ በዚያ ስፍራ የተገኙባቸውን ምክንያቶች ተናገር፡፡ በኛ ዘመን ሰዎች ኢየሱስ ወደሚገኝበት ሲመጡ አንዳንድ ምክንያቶችን ዘርዝር፡፡ አንተስ ኢየሱስ በሚገኝበት ሥፍራ ስትገኝ ከእርሱ ለመማር ወይስ የራስህ አጀንዳ አለህ?
3. በቁ3 ላይ በዚያ ሰው ሁሉ ፊት ሃጥያትዋ ሲነገር ምን ይሰማታል ብለህ ታምናለህ? እነዚህ ከሳሾችዋ ሴትየዋ ስለሚሰማት ስሜት የገደዳቸው ይመስልሃል ወይ? ለምን ይህንን እንዳልክ አስረዳ፡፡ አንተስ በህይወትህ ሕግ ብቻውን ያለ ፍቅር አደገኛ መሆኑን ምን ያህል ተገንዝበሃል?
4. በቁ4-6 ላይ ኢየሱስ ከፈሪሳውያኑ ለቀረበለት ጥያቄ አጭርና ቀላሉ መልስ ምን ነበረ? እነዚህ ሰዎች አውነት ለእግዚአብሄር ህግ ተቆርቋሪዎች መሆን አለመሆናቸውን በምን ማወቅ ይቻላል?
5. ፈሪሳውያን በተለያዩ ጊዜያት ኢየሱስን ከሙሴ ህግ ጋራ በማያያዝ ሲፈትኑት ይታያል፡፡ ለምንድነው ኢየሱስን በሌላ ነገር ከመፈተንና ከመክስ በህግ መፈተን የሚቀላቸው? አንተንስ ለመክሰስ ምክንያት የሚፈልግብህ ሰው ሊከስህ የሚችልበት ምክንያት ማግኘት ይችላል ወይስ እንደ ዳንኤልና እንደ ኢየሱስ የአምላክህ ህግ መከሰሻህ ይሆናል?
6. ቁ6-8 ሲታይ ኢየሱስ የመለሰላቸው መልስ ምን የሚል ነበረ? መልስ ከመስጠቱና ከሰጠ በኋላ ጎንበስ ብሎ በምድር ላይ የጻፈው ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል ተወያዩበት፡፡
7. ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ የሰጠው መልስ ያስከተለው ነገር ምን ነበረ? ለምን ይመስልሃል አንዳቸውም ድንጋይ ለመወርወር ድፍረት ያጡት? በሌሎች ላይ መፍረድን አስመልክቶ ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?
8. በቁ10-11 ኢየሱስ በራሱ በኩል ለሴትየዋ ያስተላለፋቸው ሁለት ግልጽ የሆኑ መልዕክቶች ምንና ምንድናቸው? ለማንኛውም በሃጥያት ለሚኖርና ወደ እርሱ ለመጣ ሰው መልዕክቱ ከዚህ የተለየ ይሆናል ብለህ ታስባህ ወይ? አንተስ መወገር የነበረብህና የእርሱን ምህረት የተቀበልክ መሆንህ ምን ያህል ገብቶሃል? ከመወገርና ከሞት ያዳነህ ኢየሱስ፤ ደግመህ በሃጥያት እንዳትኖርም እንዳዘዘህ አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሃያ ሁለት አንድ ዮሐንስ 8፡12-30

የጥናት ዓላማ፡- በዘመናችን ሁሉ የእግዚአብሄርን ፈቃድ እየመረመርንና እርሱን ደስ ለማሰኘት የምንመላለስ ከሆነ፤ እግዚአብሄር ከእኛ ጋራ እንደሆነ ሳንጠራጠር በሙሉ እርግጠኛነት መመላለስ እንደምንችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋራ ነው፣ ምንጊዜም የሚያስደስተውን ስለማደርግ ብቻዬን አልተወኝም፡፡›› ዮሐ 8፡29

1. ዮሐ 8፡12-30 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ12-13 ስንመለከት ፈሪሳውያኑ በተለይ የትኛውን ምስክርነቱን ነው ተቀባይነት እንደሌለው አድርገው የሚናገሩት? በእርሱ ለሚያምን ሰው ኢየሱስ በዚህ ክፍል የገባው የተስፋ ቃል ምንድነው?
2. ጌታ ኢየሱስ ምስክርህ ተቀባይነት የለውም ለሚለው ክሳቸው በቁ14 ላይ በመከላከያነት ያቀረበው ነገር ምን ነበረ? ዮሐ 7፡27 ስንመለከት ስለዚህ ክፍል የሚነግረን አንድ እውነት ምንድነው? ዮሐ 7፡36 እና ዮሐ 8፡22 ደግሞ ስለዚህ ክፍል ምን ያስረዱናል?
3. በብርሃን ህይወት መመላለስና በጨለማ መመላለስ ሲባል የምትረዳውን ነገር ተናገር፡፡ ከዚህ አንጻር ስለራስህ ህይወት ስታስብ በብርሃን ነው የምትመላለሰው ወይስ በጨለማ?
4. ቁ15-16 ኢየሱስ ፍርድን አስመልክቶ በአንድ በኩል አልፈርድም ይላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ፍርዴ ትክክል ነው እያለ በማለት ሁለት ተቃራኒ የሚመስሉ ሃሳቦችን መናገሩን እንዴት ታስታርቀዋለህ?
5. በቁ19 ላይ ፈሪሳውያኑ ለኢየሱስ ያቀረቡት ሌላ ጥያቄ ምን ነበረ? ኢየሱስ ለጥያቄያቸው ቀጥተኛና የጠበቁትን ዓይነት መልስ ሰጥቷቸዋል ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ፡፡
6. ኢየሱስ በቁ21 ላይ ሲናገር ‹‹እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ አትችሉም›› ያላቸው ለምንድነው? ቁ23-24 ‹‹በሃጥያታችሁ ትሞታላችሁ›› በማለት በተጨማሪ ምክንያት አድርጎ የነገራቸው ነገር ምን ነበረ? አንተስ ኢየሱስ ወደሚሄድበት መሄድ የሚያስችልህን በክርስቶስ የሚገኘውን ጽድቅ ተቀብለሃል ወይ?
7. ቁ25 ላይ የፈሪሳውያኑ ጥያቄ ምን የሚል ነው? የጌታ መልስስ? ‹‹እስካሁን የነገርኳችሁ›› የሚለው አነጋገር የሚያስረዳን ነገር ምንድነው ትላለህ?
8. ቁ29 ላይ ኢየሱስ ከእርሱ ጋራ ማን እንዳለ ነው የሚናገረው? ከእርሱ ጋራ ሁልጊዜ የሚገኝበት ምክንያት በኢየሱስ አነጋገር ለምንድነው ይላል? በየዕለት ተግባርህ ሁሉ እርሱን የሚያስደስተውን ለማድረግ ጥረት ታደርጋለህ ወይ? እግዚአብሄር ሁልጊዜ ከአንተ ጋራ እንዳለ እርግጠኛ ለመሆን ከፈለግህ ዘወትር ደስ የሚያሰኘውን ነገር እየመረመርክ ለማድረግ ትጋ፡፡

# ጥናት ሃያ ሶስት ዮሐንስ 8፡31-59

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ልጆች ለመሆናችን አንዱና ዋናው ማረጋገጫ፤ ሌሎችን የእግዚአብሄር ልጆች የሆኑትን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ማፍቀር እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ እግዚአብሄር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሄር ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም፡፡›› ዮሐ 8፡42

1. ዮሐ 8፡31-59 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ31-33 ውይይት ሲደረግ የምናየው በማንና በማን መሃል ነው? እነዚህ በቁ30 እና 31 ላይ እንዳመኑ የተነገረላቸው ሰዎች ከኢየሱስ ትምህርት ለመዋጥ ካስቸገራቸው አንደኛው የትኛው ነው?
2. ባርነት ስለሚለው ሃሳብ በቁ331-35 ስትመለከት በኢየሱስና በነዚህ አይሁዶች መሃል ያለው ያመለካከት ልዩነት ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡ ቁ32ትና ቁ36 በአንድነት ሲነበቡ ነጻ የሚያወጣው ማን ነው? አንተስ ይህንን ነጻነት አግኝተሃል ወይ? ያገኘኸውን ነጻነትስ እየተለማመድከው ነው ወይ?
3. ኢየሱስ በቁ37 ላይ እነዚህ አይሁዶች የአብርሃም ልጆች መሆናቸውን እያመነ በቁ39 ላይ ደግሞ እንዳልሆኑ በመናገሩ መሃል ያለውን ልዩነት አስረዳ፡፡ ዛሬ የተነበበውን ምንባብ ስትመለከት እነዚህ ሰዎች በእርሱ አምነዋል ወደሚለው አስተሳሰብ ያደርስሃል ወይ? ለምን?
4. በቁ31-44 ለእነዚህ ሰዎች ሊያረጋግጥላቸው የሚሞክራቸው እውነቶች ውስጥ የሚታዩህን ተናገር፡፡ ኢየሱስ ስለ አይሁዶቹ ይህንን ሁሉ ማለት የቻለው ከምን በመነሳትና ምን ያየው ነገር ስላለ ነው? የአንተስ ተግባር በመንፈስ የአብርሃም ልጅ ሊያሰኝህ የሚችል ነው ወይ?
5. ቁ44-46 ላይ ስንመለከት ኢየሱስንና ዲያቢሎስን የሚለየው አንደኛው ትልቅ ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል መሰረት ኢየሱስ ሊከሰስ የማይችልበት አንድ ነገር ምንድነው?
6. ኢየሱስና አይሁዶቹ በቁ48-53 ያካሄዱት ሌላው የውይይት ርዕስ ያተኮረው በምን ላይ ነበረ? ኢየሱስ ጋኔን እንዳለበት ማረጋገጫ ነው ብለው ያሰቡት ነገር ምንድነው?
7. ቁ49 ‹‹እናንተ ታዋርዱኛላችሁ›› ቁ54 ‹‹የሚያከብረኝ…አባቴ ነው›› የኢየሱስ ክብርና ውርደት የመጣው ከየት ነው? ኢየሱስ በሰዎቹ በመዋረዱ ያስከተለበት ምን ስሜት ይታይሃል? ለምን? አንተስ ክብርን የምትፈልገው ከሰዎች ወይስ ከእግዚአብሄር?
8. እነዚህ አይሁዶች በመንፈስ የአብርሃም ልጆች ማለትም ከእግዚአብሄር ላለመሆናቸው በተለይ በቁ42 ላይ የተጠቀመበት ማረጋገጫ ምን ነበረ? አንተስ የእግዚአብሄር ልጅ ለመሆንህ ማረጋገጫ የሚሆነው ፍቅር በህይወትህ ትለማመደዋለህ ወይ? 1ኛ ዮሐ 2፡9-11 የእግዚአብሄር ልጅነትህ የምታረጋግጥበት  አንዱ መንገድ ሌሎቹን ወንድሞችህንና እህቶችህን በማፍቀርህ መሆኑን ልትገነዘብ ይገባሃል፡፡

# ጥናት ሃያ አራት ዮሐንስ 9፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- በዙሪያችን ያሉት ሁሉ ኢየሱስን በሚያቋሽሹበትና በሚያራክሱበት ሥፍራ ስንገኝ፤ የኢየሱስን እውነተኛ ማንነትና ያደረገልንን መናገር እንድንችል ጌታ ጸጋን እንዲያበዛልን መጸለይ እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ፣ ዓይነ ስውር ወደ ነበረው ሰው ተመልሰው፣ ዓይንህን ስለከፈተው ሰው እንግዲህ አንተ ምን ትላለህ? አሉት፡፡ ሰውየውም እርሱ ነብይ ነው አለ፡፡›› ዮሐ 9፡17

1. ዮሐ 9፡1-17 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ የደቀመዛሙርቱ ጥያቄ ምን ነበረ? ይህ ጥያቄ የመነጨው ከምንድነው ብለህ ታስባለህ?
2. ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው መልስ ምን የሚል ነው? ሁልጊዜ ሰዎች ሲታመሙ ለእግዚአብሄር ክብር ወይም ሥራው በህይወታቸው ሊገለጥ ነው ማለቱ ነው ወይ? አስረዳ፡፡ በዚህ ክፍል ከምናየው ከደቀመዛሙርቱ ስህተት መማር የምንችለው ነገር ምንድነው?
3. በቁ6-7 ላይ ኢየሱስ ሲያደርግ የምናየው ነገር ምንድነው? ሰውየውስ የወሰደው እርምጃና ውጤቱ ምን እንደነበረ ተናገር፡፡ ይህ ሰው ያደረገው ነገር በብሉይ ኪዳን ከምናየው ከንእማን በምን ይለያል ትላለህ?
4. ቁ8-11 ዓይኑ በበራለት ሰው ማንነት ላይ ለተነሳው ክርክር የተሰነዘሩት ሶስት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ጎረቤቶቹ ለእርሱ የነበራቸው ጥያቄ ምን ነበረ? ሰውየው የመለሰው ምን በማለት ነው? አንተስ ብትጠየቅ እንደዚህ ሰው በህይወትህ ኢየሱስ እንዴት እንዳዳነህና የዘላለም ህይወትን እንደሰጠህ አንድ በአንድ መናገር ትችላለህ ወይ?
5. ቁ12-14 ስናነብ ይህ ሰው ኢየሱስ የት እንዳለ ሲጠየቅ እንደማያውቅ መናገሩ ለምንድነው ብለህ ታስባለህ? ሰዎቹ ሰውየውን ወደ ፈሪሳውያን የወሰዱበት ምክንያት ምን ነበረ? ቁ14 ኢየሱስ በሰንበት ሁለት ጥፋት እንዳጠፋ ይመስላል፤ እስቲ የሚታይህን ሁለት ነገሮች ከቁ14 ላይ ተናገር፡፡
6. በቁ10ላይ ለጎረቤቶቹ እንደመሰከረ በቁ15 ላይ ደግሞ ስለየሱስ ስራ እንዲናገር የተከፈተለት ለማን ነበረ? ለጎረቤቶቹም ሆነ ለሃይማኖት መሪዎቹ የእርሱ ምስክርነት ምን ነበረ?
7. ኢየሱስ በዚህ ሰው ላይ የሰራው ተአምር በፈሪሳውያኑ መሃል ምን ሲፈጥር ነው የምንመለከተው? እነዚህ ሰዎች የተለያዩባቸውን ምክንያቶች አስረዳ፡፡ አንተ በእነርሱ መሃል ተገኝተህ ሃሳብ መስጠት ቢኖርብህ ሃሳብህ ምን ይሆን እንደነበረ ግለጽ፡፡
8. በቁ17 ላይ ይህ እውር የነበረ ሰው ስለ ኢየሱስ ማንነት እንዲናገር እድል ሲሰጠው እናያለን፡፡ ለተጠየቀው ጥያቄ ይህ ሰው የመለሰው መልስ ምን የሚል ነው? ፈሪሳውያኑ ምን ዓይነት መልስ የጠበቁ ይመስልሃል? ተቃዋሚዎች በበዙበት መሃል ስለ ኢየሱስ ማንነት ለመናገር ድፍረት አለህ ወይ? ስለ ኢየሱስ መልካም የሚናገር አንድ ሰው እንኳን በማይገኝበት ሥፍራ ስለስሙ ለመናገር የምታገኘውን እድል በመጠቀም ለመናገር እንድትችል ጸጋ እንዲያበዛልህ ጌታን ለምን፡፡

# ጥናት ሃያ አምስት ዮሐንስ 9፡18-29

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ በህይወታችን የሰራውን የደህንነት ሥራ እንድንጠራጠር በተለያየ መንገድ ጠላት የጥያቄውን ውርጅብኝ ሊያመጣብን እንደሚችልና፤ እኛም ደግሞ እውሩ ሰው እንደመለሰው ‹ሃጥያተኛ እንደነበርኩ አሁን ግን ምህረትን እንደተቀበልኩ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ›› ማለት እንደምንችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አንተ ሰው እግዚአብሄርን አክብር፤ ይህ ሰው ሃጥያተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን አሉት፡፡ እርሱም ሃጥያተኛ መሆኑን እኔ አላውቅም፤ ነገር ግን ዓይነ ስውር እንደነበርሁ፤ አሁን ግን እንደማይ ይህንን አንድ ነገር አውቃለሁ አለ፡፡›› ዮሐ 9፡24-25

1. ዮሐ 9፡18-29 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ18-19 ላይ ዓይኑ የበራለት ሰው ወላጆቹ እንዲጠሩ ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው? ወላጆቹ ሲመጡ የተጠየቋቸው ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ናቸው?
2. ወላጆቹ በቁ20-21 ላይ በሰጡት መልስ ስለልጃቸው የሚያውቋቸው ሁለት ነገሮችና የማያውቋቸው ሁለት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአይሁድ የነገሯቸው ነገር ምን ነበረ? ይህ አነጋገር በተለይ ስለሌሎች ሰዎች መናገር የማያስፈልግ ነገር ስንጠየቅ እንዴት ሊጠቅመን እንደሚችል ተወያዩበት፡፡
3. በቁ22-23 መሰረት ወላጆቹ ለአይሁድ ጥያቄ የሰሙትን ወይም የራሳቸውን አመለካከት ሳይናገሩ ወደ ልጃቸው ስላስተላለፉበት ምክንያት ምን ይነግረናል? ከዚህ ክፍል ስንመለከት ወላጆቹ ስለኢየሱስ ምን አመለካከት እንዳላቸው ነው የሚጠቁመን? በአንተ አመለካከት እነዚህ ሰዎች ያደረጉት ነገር ጥበብ ነው ወይስ ፍርሃት? ተወያዩበት፡፡
4. አይሁድ በድጋሚ ማወቅ የፈለጉትና በቁ26 ላይ ሰውየውን የጠየቁት ጥያቄ ምን ነበረ? በቁ27 ላይ የሰውየው መልስ ሊጠቁመን የሚችለው ነገር ካለ ምንድነው ትላለህ?
5. አይኑ የተከፈተለት ሰው በቁ27 ላይ ለጠየቃቸው ጥያቄ የአይሁድ ምላሽ ምን ነበረ? ሰዎችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ እንዲሆኑና የወንጌልን እውነት እንዲቀበሉ ስትናገር ይህ ሰው የተቀበለውን አይነት የስድብ ናዳ ለመቀበል ምን ያህል ልብህን አዘጋጅተሃል?
6. እነዚህ አይሁዶች በቁ24 ላይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለነበራቸው አመለካከት ምን እንረዳለን? ይህ ሰው በዚህ ክፍል ውስጥ ምን እንዲያደርግ ሲጠየቅ ነው የምናየው?
7. በምዕ 9 በቁ10፣15፣17፣24 እና 26 ላይ እነዚህ ሰዎች በተደጋጋሚ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ሲጠይቁት ይታያል፤ አይሁዶቹ ከዚህ ሰው አፍ መስማት የፈለጉት ነገር ምንድነው ብለህ ትገምታለህ? በቁ25 ላይ የምናነበው የሰውየው ምላሽ ምን የሚል ነው?

# ጥናት ሃያ ስድስት ዮሐንስ 9፡30-41

የጥናት ዓላማ፡- ምንም ያህል የቃሉ እውቀት ቢኖረንና ሌሎችን እንኳን የምናስተምር ብንሆን፤ ከሌሎች ልምድና እውቀት ላለመቅሰም አዕምሯችንን መዝጋት ኢየሱስን እንኳን ማየት እንዳንችል እንቅፋት ሊሆንብን እንደሚችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እነርሱም፣ ሁለንተናህ በሃጥያት ተነክሮ የተወለድህ፣ አንተ እኛን ለማስተማር እንዴት ትደፍራለህ? ሲሉ መለሱለት፤ አባረሩትም፡፡›› ዮሐ 9፡34

1. ዮሐ 9፡30-41 ያለው በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ30 ስናነብ ከላይ በቁ29 ላይ አይሁድ ከተናገሩት ንግግር ሁሉ ይህንን እውር የነበረ ሰው ያስደነቀው አንድ ነገር ምን ነበረ? አለማወቃቸው ይግረመው እንጂ ለእርሱ ግን ዋነኛ ነገር ሆኖ ያየው ነገር ምንድነው ይላል?
2. ለምንድነው ብለህ ታምናለህ የነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ከየት እንደመጣ አለማወቃቸው ከእውርነት የተፈወሰውን ሰው ያስደነቀው?
3. በቁ31-32 ስንመለከት ይህ ሰው በሁለት መንገዶች እነዚህን ተጠራጣሪዎች ሊያሳምን ይሞክራል፤ እነዚህ ሁለት መንገዶች ምንና ምንድናቸው? በሰውየው አነጋገር እግዚአብሄር የሚሰማው ምን ዓይነት ሰዎችን ነው?
4. ቁ31-33 ትን ስናይ ሰውየው ስለ ኢየሱስ ማንነት የደረሰባቸው ቢያንስ ሶስት እውነቶችን ተናገር፡፡ በአንተ ልብ ውስጥስ ስለኢየሱስ እነዚህን ሶስት እውነቶች ምን ያህል በእርግጠኛነት ታምናቸዋለህ?
5. በቁ35-36 የተካሄደውን ሁኔታ ለአንተ በገባህ መንገድ ለሌሎች ተናገር፡፡ የኢየሱስ ጥያቄ ለሰውየው ምን የሚል ነበረ? የሰውየው መልስ ምን የሚል ነው? አንተስ የምታምንበትን የኢየሱስን ማንነት ለማወቅ ሁልጊዜ መጠየቅና ጥረት ማድረግ እንደሚኖርብህ ምን ያህል ተረድተሃል?
6. ቁ37-39 ባለው ክፍል ውስጥ ሰውየው የኢየሱስን ማንነት ባወቀና በተገለጠለጥ ጊዜ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? የኢየሱስ ማንነት ስናይና ራሱን ሲገልጥልንና የእኛም ምላሽ ይህ ሊሆን ይገባል፡፡ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ስለመጣበት ምክንያት በዚህ ክፍል የተናገረው ምን በማለት ነው?
7. ይህ በቁ39 ላይ ኢየሱስ የተናገረው ንግግር በፈሪሳውያኑ ውስጥ ያስከተለው ጥያቄ ምን ነበረ? ፈሪሳውያኑ ለጠየቁት ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው መልስ ምን ነበረ? በኢየሱስ አነጋገር ከእውርነት ይልፈቅ መጥፎው በሽታ ምንድነው? ይህ በሽታ በአንተ ላይ እንዳይሰለጥን ልትጠነቀቅ ይገባሃል፡፡
8. መለስ ብለን ቁ34ትን ስንመለከት እነዚህ ሰዎች ሊቀበሉት ያልቻሉት አንድ ነገር ምን ነበረ? አንተስ የተናቁ ከሚመስሉ ሰዎች የእግዚአብሄርን እውነትና ከልምዳቸው ለመማር ምን ያህል ልብህ የተዘጋጀ ነው? ምንም ያህል የቃሉ እውቀት ቢኖርህና አስተማሪም ብትሆን ከሌሎች ልምድና እውቀት ለመቅሰም ልብህ ዘወትር የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል፡፡

# ጥናት ሃያ ሰባት ዮሐንስ 10፡1-21

የጥናት ዓላማ፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት፣ ማንም በግድና በሃይል አሸንፎት ለመስቀል ያበቃው ሳይሆን፤ ራሱ ወዶ በፈቃደኛነት ህይወቱን መስዋዕት አድርጎ ለሰው ልጆች እንደሰጠ ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ህይወቴን በራሴ ፈቃድ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፤ አሳልፌ ለመስጠትም ሆነ ለማንሳት ሥልጣን አለኝ፤ ይህን ትዕዛዝ የተቀበልኩት ከአባቴ ነው፡፡›› ዮሐ 10፡18

1. ዮሐ 10፡1-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ላይ እያወዳደረ የሚናገረው ማንንና ማንን ነው? ለእረኛ መለያ ሆነው የተነገሩትን ሃሳቦች ተንትነህ ተናገር፡፡
2. በተለይ በቁ4-5 ውስጥ ለበጎቹ አንደኛውን ለመከተልና ሌላኛውን ግን ላለመከተል ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የተጠቀሰው ነገር ምንድነው? እንግዳ ለሆነው ነገር የበጎቹ አቀባበል በቁ5 ላይ ምን ይመስላል? አንተስ የእረኛህን ድምጽ በዙሪያህ ከሚሰማው ከተለያየ ድምጽ ለይተህ ታውቀዋለህ ወይ? እንግዳ ከሆነና ከእረኛህ ያልሆነውን ነገርስ ካለመከተልም አልፈህ ሸሽትም እንደሚያስፈልግ ተረድተሃል ወይ?
3. በቁ7 ጀምሮ ያለውን ሃሳብ ኢየሱስ መናገር ያስፈለገው በምን ምክንያት ነው ትላለህ? ቁ7-10 ላይ ኢየሱስ ራሱን በምን መስሎ ነው ያቀረበው? በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መግባት የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ሆነው የተጠቀሱትን ነገሮች በመዘርዘር ተናገር፡፡
4. ቁ10 ኢየሱስ ራሱን ሲያነጻጽር የምናገኘው ከማን ጋራ ነው? ሌባው ስለሚመጣበት ምክንያት የተነገሩን ሶስት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? ኢየሱስስ ስለመጣበት ምክንያት ከዚህ ቁጥር ምን ትመለከታለህ? ሰይጣን ሰላምህን ሊሰርቅ፣ ራዕይህን ሊገድልና ብርሃንህን ሊያጠፋና ሊያጨልም ዘወትር እንደሚጥር ታውቃለህ? ኢየሱስ ግን የተትረፈረፈ ህይወት እንዲኖርህና እንዲበዛልህ መጥቷል፡፡
5. በቁ11-13 ላይ ኢየሱስ 3ራሱን እንደማን አድርጎ ነው የሚያቀርበው? ራሱንስ ከማን ጋራ ሲያነጻጽር ነው የምናገኘው? በዚህ ክፍል የኢየሱስና የተቀጣሪው እረኛ በዚህ ክፍል የተነገሩን መለያዎቻቸው ምንድናቸው? ተቀጣሪው እረኛ ቆሞ ከተኩላ ጋራ ለመጋፈጥ የማይፈልግበት ምክንያት ለምንድነው? የአንተ እረኛ ጥሎህ የሚሸሽ ነው ወይስ ህይወቱን እስኪሰጥ የሚሞትልህ?
6. ቁ14-15 ስናነብ በተለይም በቁ14 ላይ በበጎችና በእረኛቸው መሃል የሚታየው የጋራ ነገር ምንድነው? ይህንን መተዋወቅ በቁ15 ላይ የሚያነጻጽረው ከምን ጋራ ነው? እረኛው ብቻ ወይም በጎቹ ብቻ ሳይሆን በሁለቱም በኩል መተዋወቅ መኖሩ ምን ሊያስተምረን ይችላል ትላለህ?
7. ቁ16 ኢየሱስ የሚናገረው ስለነማን ነው ብለህ ታምናለህ? በዚህ ቁጥር ላይ አሉኝ በሚላቸውና ከላይ ባሉት ቁጥሮች ላይ በተጠቀሱት በጎቹ መሃል የሚታየው አንድ ተመሳሳይነት ምንድነው? ለአማኞች ስንት እረኛ አለ? ኢየሱስስ በዚህ ክፍል መሰረት ስንት መንጋ ነው ያለው?
8. ቁ19-21 ስናነብ ኢየሱስ ከተናገረው መሃል በአይሁድ ዘንድ መከፋፈልን የፈጠረው ማዕከላዊ ሃሳብ የትኛው ትላለህ? ክፍፍሉን ስታይ ሁለቱ የያዙአቸው ሃሳቦች ምንና ምን የሚሉ ነበሩ?
9. ኢየሱስ ስላሚሟቱ በቁ17-18 ላይ ምንድነው የሚነግራቸው? ኢየሱስ ስልጣን አለኝ ሲል ስልጣኑ ምን ምን ማድረግን ያካትታል? ኢየሱስ ወዶ ማንም ሳያስገድደው ራሱን ላንተ እንደሰጥ ተረድተሃል ወይ? ጌታ አንተን ለማዳን ለመስቀል ሞት የበቃው በፈቃደኛነት እንጂ በመሸነፍ እንዳልሆነ ልትረዳ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት ሃያ ስምንት ዮሐንስ 10፡22-42

የጥናት ዓላማ፡- ህይወት የሰጠን፣ እንደማንጠፋ ቃል የገባልንና፣ ከእጁ ማንም አይነጥቃችሁም ያለውን ጌታ በመታመን በፈቃዱ ውስጥ የሚኖር ሰው የመጥፋት ፍርሃት ሊያስጨንቀው እንደማይገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እኔ የዘላለም ህይወት እሰጣቸዋለሁ፣ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም፡፡ እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴ እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም፡፡›› ዮሐ 10፡28-29

1. ዮሐ 10፡22-42 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ22-24 ላይ አይሁድ የኢየሱስን ማንነት አስመልክቶ ስላሉበት ሁኔታ ምን ያስረዳናል? የነዚህ ሰዎች ጥያቄ ምን የሚል ነው?
2. የኢየሱስ መልስ በቁ25-27 ላይ የሚል ነበረ? እነዚህ የሚናገራቸው አይሁድ ስለማያምኑበት ምክንያት ኢየሱስ አስረግጦ የነገራቸው ነገር በዚህ ክፍል ምን ነበረ? ለእርሱ በጎች መለያ አድርጎ የሚናገው ነገር ምንድነው?
3. በቁ31-33 ላይ ኢየሱስን በድንጋይ ሊያስወግረው የነበረው ከተናገረው ሃሳብ የትኛው ነው? ኢየሱስ ሊወግሩት ለተነሱት ለአይሁድ ያቀረበላቸው ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? እነዚህ ሰዎች ‹‹የስድብ ቃል ስለተናገርህ›› ማለታቸው ምን ለማለት ፈልገው ይመስልሃል?
4. ቁ34-36 ላይ ስንመለከት መጽሐፍ ቅዱስን አስመልክቶ አንድ የሚያረጋግጥልን እውነት ምንድነው? በዚሁ ክፍል ውስጥ ስለኢየሱስ ማንነትስ የሚነግረን እውነት ምንድነው ትላለህ? በአጠቃላይ ኢየሱስ ለአይሁድ የሰጠውን መልስ በምን መንገድ ነው የምትረዳው? ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የአንተስ አቋም ይህንን ያህል ጠንካራ ነው ወይ?
5. ቁ37-39 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ ተቃዋሚዎቹ እንዳይናገር የፈለጋቸውን ነገሮች መናገሩን እንዳልተወ የመንመለከተው እንዴት ነው? ለምን ይመስልሃል ኢየሱስ በትምህርቱ የጸናው? ሰዎቹስ ስለኢየሱስ ሃሳባቸውን አለመቀየራቸው በምን እናያለን? አንተስ ሰዎች ስለተቃወሙ ብቻ እውነት እንደሆነ አውቀህ የያዝከውን ወይም የምታስተምረውን እውነት ትጥላለህ ወይ?
6. ተአምራትን አስመልክቶ ስለዮሐንስ በዚህ ክፍል የተነገረው ነገር ምንድነው? ዮሐንስ ስለኢየሱስ ስለተናገረው ነገርስ እነዚህ ሰዎች ምን ይላሉ? ሰዎች እንዲናገሩልህ የምሻው በአንተ ስለሚደረገው ተአምራት ነው ወይስ ውሸትን የማያውቅ እውነተኛ ሰው ነው መባል?
7. በቁ28-29 ኢየሱስ ስለበጎቹ የሚናገራቸውን ነገሮች በሙሉ በዝርዝር ተናገር፡፡ በጎቹ በዚህ ክፍል መሰረት የተያዙት በማን እጅ ነው? በእውነት ደህንነትን የተቀበለ አማኝ በዚህ ክፍል መሰረት መስጋት የማይኖርበት ለምንድነው? ስለደህንነትህ ስጋት አለህ ወይ? በአብና በወልድ እጅ የተያዝክ ስለሆነ ከእጁ ፈልቅቆ ሊያስወጣህ የሚችል ሃይል ስለሌለ በእምነትህ በርታ፡፡

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ ዮሐንስ 11፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- የእኛ የራሳችንና የሌሎችም እምነት እንዲያድግ፤ እግዚአብሄር እጅግ ቢወደንም በህይወታችን ለጊዜው የማንፈልገውና የማይስማማን ሁኔታ እንድንገባ ሊፈቅድ እንደሚችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ኢየሱስም ማርታን፣ እህቷንና አልዓዛርን ይወዳቸው ነበር፡፡ ሆኖም አልአዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቆየ፡፡›› ዮሐ 11፡5

1. ዮሐ 11፡1-16 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ውስጥ የምታያቸውን ተዋናኞች ሁሉ ዘርዝር፡፡ ይህ ክፍል በተለይም ማርያምን እንዴት አድርጎ ነው የሚያስተዋውቀን? ለምን ይመስልሃል ጸሐፊው ይህችን ሴት በዚህ መልክ ማስተዋወቅ የፈለገው?
2. ቁ3-4ትን ስናነብ ለኢየሱስ የደረሰው መልዕክት ምን የሚል ነበረ? ኢየሱስ ለደረሰው መልዕክት ምላሹ ምን የሚል ነበረ? በምላሹ ውስጥ የኢየሱስን አምላክነት የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው?
3. ደቀመዛሙርቱ በቁ7-10 ላይ ኢየሱስን ወደ ይሁዳ እንዳይሄድ ሲያከላክሉት የሚታዩት ምን ምክንያት በመስጠት ነው? ከኢየሱስ አነጋገርስ ምን ትረዳለህ?
4. ኢየሱስ የአልዓዛርን ሞት በቁ11-12 ላይ ለደቀመዛሙርቱ ያቀረበላቸው ምን በማለት ነው? ይህንን ሲናገር ደቀ መዛሙርቱና ኢየሱስ ያልተግባቡት ለምን ይመስልሃል? አንተስ የቅዱሳን ሞት እንቅልፍ እንደሆነ እውነት ተረድተሃል ወይ?
5. ቁ13 መሰረት ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ አልአዛርን ከእንቅልፍ ለማስነሳት መሄድ ብለው ማሰባቸው ስሜት የማይሰጠው ለምንድነው? ለዚህ አይነቱ አመለካከት ያደረሳቸው ነገር ምንድነው ብለህ ታስባለህ?
6. ቁ14-16 በማንበብ ኢየሱስ በቁ6 ላይ መልዕክቱ ሲደርሰው ወዲያው ያለመሄዱ አንደኛው ምክንያት ሆኖ በዚህ ክፍል የምናየው ምንድነው? እውነቱ ከገባው በኋላ የቶማስ ውሳኔ ምን ነበረ? ሰዎች ከዘለዓለም ሞት እንዲተርፉ የህይወት ጌታ የሆነውን ኢየሱስን ወደ እነርሱ ለመውሰድ አንተስ ምን ያህል ቆርጠሃል?
7. መለስ ብለን ቁ5-6ትን ስናነብ በነማርያም ቤተሰብና በኢየሱስ መሃል ስላለው ግንኙነት የምንረዳው ነገር ምንድነው? ኢየሱስ ይወደው የነበረው ሰው መታመሙን ሲሰማ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ለምን ይመስልሃል ይህንን ያደረገው?
8. በህይወትህ አስቸጋሪና ከባድ ሁኔታ ሲገጥምህ ጠላት እግዚአብሄር እንደማይወድህ በጆሮህ ሹክ ብሎልህ ያውቃል ወይ? እግዚአብሄር የአንተና በአካባቢህ ያሉት ወገኖች እምነት እንዲያድግ በህይወታችን ከባድና አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዲመጡ ሊፈቅድ እንደሚችልና ያ ማለት ላንተ ያለው ፍቅር ተለውጧል ማለት እንዳልሆነ ልትረዳ ይገባሃል፡፡

# ጥናት ሰላሳ ዮሐንስ 11፡17-37

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ ለወዳጁ ለአልአዛር እንባውን እንዳፈሰሰና እንዳዘነ ሁሉ እኛም ወዳጅና ዘመዶቻችን በሞት ሲለዩን ስርዓት ባለው መንገድ የማልቀስና የማዘን ነጻነት እንዳለን ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የት ነው ያኖራችሁት ሲል ጠየቀ፡፡ እነርሱም ጌታ ሆይ መጥተህ እይ አሉት፡፡ ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ አይሁድም እንዴት ይወደው እንደነበረ አያችሁ አሉ፡፡›› ዮሐ 11፡34-36

1. ዮሐ 11፡17-37 በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ የምታያቸውን ተዋናኞች በሙሉ ዘርዝር፡፡ ኢየሱስ ቢታንያ ሲደርስ የአልአዛር ሁኔታ ምን ይመስል ነበረ?
2. የኢየሱስን መምጣት አስቀድሞ የሰማው ማን ነበረ? ማርታና ማርያም ቤት ውስጥ ለማጽናናት የተሰበሰቡ ሰዎች እያሉ ለምንድነው ኢየሱስን ወጥተው መቀበል ያስፈለጋቸው?
3. በቁ21-22 ላይ ማርታ ለኢየሱስ የነገረቻቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ከዚህ አነጋገሯ ኢየሱስን ወስናዋለች ማለት የሚቻለው በምን መንገድ ነው? አንተስ ኢየሱስን የምትወስንባቸው ሁኔታዎች አሉህ ወይ?
4. በቁ23-26 ላይ በተካሄደው ውይይት ‹‹ወንድምሽ ይነሳል›› የሚለውን የኢየሱስ አነጋገር ማርያም የተረዳችው በምን መንገድ ነው? በትንሳኤ ቀን ማለትም ለብዙ አመታት ቆይቶ ከበሰበሰና ከሸተተ በኋላ አልአዛር ይነሳል ብሎ ከማመንና፤ ዛሬውኑ ኢየሱስ ወንድሜን ያስነሳዋል ብሎ ከማመን የትኛው ይቀላል ብለህ ትላለህ? ለምን?
5. በቁ26 ላይ ‹‹…የሚያምንብኝ ከቶ አይሞትም›› ሲል ኢየሱስ የሚናገረው ስለምን ዓይነት ሞት ነው? ኢየሱስ ስለ ትንሳኤና ህይወት ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
6. ቁ28-29 ማርታ ከኢየሱስ ጋራ ንግግሯን ስትጨርስ ያደረገችው ነገር ምንድነው? ማርያም የኢየሱስ መምጣት ሲነገራት የወሰደችው እርምጃ ምንድነው? ኢየሱስ በሃዘን ተቆራምዳ ያለችውን ሴት መፈለጉና ያለችበት ድረስ ለመምጣት መፍቀዱ ለራስህ ህይወት ምን ያስተምርሃል?
7. ቁ36-37 አይሁድ የተናገሯቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በተለይ በቁ37 ላይ የሰነዘሩት ሃሳብ በቁ21 እና 32 ላይ እህትማቾቹ ከተናገሩት ንግግር ጋራ ተመሳሳይነት ያለው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡
8. በቁ36 ላይ አይሁድ የተናገሩትን ለመናገር ያበቃቸው ነገር ምንድነው? ወዳጅ፣ ቤተሰብ፣ ጓደኛና የመሰሰሉት በሞት ሲለዩህ ለምታሳየው ስሜት ይህ ክፍል በምን መንግድ ይረዳሃል? ወዳጆች በሞት ሲለዩን የማልቀስና ስሜታችንን የመግለጽ ነጻነት እንዳለን ከኢየሱስ ስንማር፤ ከልክ ያለፈ ሃዘን ግን ቃሉ እንደማይደግፍ ከ1ኛ ተሰ 4፡13 መማር እንችላለን፡፡

# ጥናት ሰላሳ አንድ ዮሐንስ 11፡38-57

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ አልአዛርን ከሙታን ካስነሳው በኋላ በነጻነት እንዳይንቀሳቀስ ተብትቦ የያዘው ነገር እንዲፈቱት እንዳዘዘ ሁሉ፤ እኛም በጌታ አዲስ ህይወትን የተቀበልን፤ ለተጠራንበት ጥሪ እንደሚገባ በነጻነት ለመመላለስ እንዳንችል ከሚያስረን የሥጋ ሥራ ሁሉ መፈታትና ነጻ መሆን እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ኢየሱስም ‹‹መግነዙን ፍቱለትና ይሂድ›› አላቸው፡፡ ዮሐ 11፡44

1. ዮሐ 11፡38-57 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ38-40 ላይ ስናነብ ኢየሱስ በዚያ የነበሩትን ሰዎች ያዘዛቸው ነገር ምን ነበረ? ለምን ይመስልሃል ራሱ ማድረግ ሲችል እነርሱ እንደያደርጉት ያዘዛቸው? ለኢየሱስ ትዕዛዝ የማርያም ምላሽ ምን ነበረ? ኢየሱስ ባይነካካው ይሻላል ብለህ የምትለው የሸተተ ነገር በህይወትህ ይኖር ይሆን?
2. በቁ40 ላይ ‹‹ብታምኚስ የእግዚአብሄርን ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርኩሽምን?›› ብሎ የሚያስታውሳት የትኛውን ሃሳብ ነው ትላለህ? በቁ25-26 ላይ የተናገራት ንግግር አሁን ማርታ ለሰጠችው ሃሳብ መልስ የሚሆነው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡
3. ቁ41-43 ሰዎቹ ድንጋዩን ካነሱ በኋላ ኢየሱስ ያደረጋቸውን ነገሮች ተናገር፡፡ በቁ42 ላይ ‹‹ይህን መናገሬ ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደላከኝ ያምኑ ዘንድ ነው›› ማለቱ ምን ማለት እንደሆነ የምትረዳውን ተናገር፡፡
4. ቁ45-47 ኢየሱስ ያደረገው ተአምራት በተመለከቱት ሰዎች ህይወት ውስጥ ምን ያስከተለው ነገር ታያለህ? ይህንን የመሰለ ታላቅ ተአምራት ተደርጎ እያዩ ለምንድነው እዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ያላመኑት? ከዚህ ሁኔታ ምን ትማራለህ?
5. ቁ47-50 የፈሪሳውያኑ ችግር ምን ነበረ? በመፍትሄነት የቀረበው ሃሳብ ምን የሚል ነው?
6. ቁ50-53 ቀያፋ ስለኢየሱስ የተናገረውን ንግግር ትንቢት አድርገን ልናይ የምንችልበት ምክንያት ለምንድነው? ‹‹ይህንን ያለው ከራሱ አልነበረም›› ሲል ጸሃፊው ምን ማለቱ ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ የኢየሱስ ሞት ከአይሁድ ውጭ ሌሎችንም እንደሚያካትት የሚጠቁም ምን ሃሳብ ታያህ?
7. ቁ53 እና 57ትን ስንመለከት ፈሪሳውያን በኢየሱስ ላይ ስላላቸው አመለካከት ምን ያሳየናል? የህግ አስተማሪዎች ሆነው ሰውን ወደመሲሁ መምራት ሲገባቸው ወደዚህ አይነቱ ተግባር መሰማራታቸው ምን ያሳይሃል?
8. በቁ41 ላይ ድንጋዩን እንዲያነሱ ያዘዘው ኢየሱስ፤ በዚህ ቁጥር ላይ ያዘዛቸው ምን በማለት ነው? ለምንድነው አልዓዛር መፈታት የሚያስፈልገው? በዕብ 12፡1 ላይ እንደሚናገረው ‹‹ሸክም የሚሆንብንን በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ሃጥያት አስወግደን›› እንደሚለው አንተም ነጻነትህን ጠብቀህ መኖር እንድትችል መንፈስ ቅዱስ በየዕለቱ እንዲፈታህ ለቃሉ መታዘዝና መገዛት እንደሚኖርብህ ዘወትር አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሰላሳ ሁለት ዮሐንስ 12፡1-19

የጥናት ዓላማ፡- እንደ አልዓዛር ሌሎች ኢየሱስን ሲያገለግሉ ዳር ተቀምጠን የምንመለከት ሳንሆን፤ ከማንም ያላነሰ ብዙ የተደረገልና የዘለዓለም ህይወት የተሰጠን ስለሆንን እኛም ባለን ሃይላችን ሁሉ ከወገኖቻችን ጎን ተሰልፈል በሙሉ ሃይላችን ልናገለግለው እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹በዚያም ለኢየሱስ ሲባል ራት ተዘጋጀ፡፡ ማርታ ስታገለግል፣ አልዓዛር ከእርሱ ጋር በማእድ ከተቀመጡት አንዱ ነበረ፡፡›› ዮሐ 12፡2

1. ዮሐ 12፡1-19 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-3 ላይ የምታያቸውን ሰዎች ዘርዝር፡፡ በነዚህ ቁጥሮች የተካሄደውን በአጭሩ በራስህ ቋንቋ ለወገኖች ተናገር፡፡
2. በቁ3 ላይ ማርያም ያደረገችው ድርጊት በቁ4-6 ስናነብ ያስከተለው ነገር ምን እናያለን? ይህንን ሁኔታ በዋነኛነት እንደጠየቀ የተነገረለት ማን ነበረ? ዮሐንስ በዚህ ላይ ለአንባቢዎቹ የሰነዘረው ሃሳብ ምን የሚል ነበረ?
3. ከይሁዳ ለተዘነዘረው ተቃውሞ በቁ7-8 ላይ የኢየሱስ ምላሽ ምን የሚል ነበረ? የሽቶው ዋጋ ለአንድ ሰው የአመት ደመወዝ እንደሚሆን ይናገራሉ፡፡ ይሁዳ የተናገረው ነገር ምንም ስሜት አይሰጥም ማለት ነው ወይስ የኢየሱስን አባባል የምትረዳው እንዴት ነው? ሰዎች ለጌታ የሚያደርጉት ሞኝነት የሚመስልህ ነገር ገጥሞህ ያውቃል? አንተስ ለኢየሱስ ሰዎች ሞኝነት የሚሉትን ነገር ለማድረግ ምን ያህል ድፍረት አለህ?
4. ቁ9-11 ለምን ነበረ ብዙ አይሁድ ወደ ኢየሱስ የመጡት? በዚህ ክፍል ውስጥ የብዙ ሰዎች ወደኢየሱስ መምጣት ያስከተለው ነገር ምን ታያለህ? አልዓዛር በነዚህ ሰዎች ህይወት ምን አስተዋጽዖ ነበረው?
5. ቁ12-16 ላይ እየሆነ ያለውን ነገር በአጭሩ ተናገር፡፡ ጌታ የሱስ ይህንን ድርጊታቸውን እንደተቀበለው የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው?
6. ቁ17-19ን ስታነብ ስለኢየሱስ ሥራ ይመሰክሩ የነበሩት ሰዎች እነማን ናቸው? በቁ12-16 ለብዙዎች የደስታ ጊዜ ሲሆን፣ የሃዘን ጊዜ ሆኖ የተገኘው ለማን ነው? ከፈሪሳውያኑ አነጋገር ኢየሱስን ስለተከተሉት ሰዎች ቁጥር ምን መረዳት ትችላለህ?
7. መለስ ብለን ቁ2ተን ሌሎች ኢየሱስን ሲያገለግሉ ታላቅ ነገር የተደረገለት አልዓዛር ምን ሲያደርግ ነው የምንመለከተው? አንተስ ሌሎች ለኢየሱስ ሲሯሯጡና የመንግስቱን ሥራ ሲሰሩ ተቀምጠህ ተመጋቢ ብቻ ነህ ወይ? 1ኛ ቆሮ 15፡58 እንደሚናገረው አንተም ከሞት ባርነት ነጻ የወጣህ ስለሆነ ተቀማጭ ሳትሆን ለጌታ ስራ ዘወትር የሚበዛልህ ልትሆን እንደሚገባህ አትዘንጋ፡፡

# <u>ጥናት ሰላሳ ሶስት ዮሐንስ 12፡20-50</u>

የጥናት ዓላማ፡- ሰዎች ወደ እግዚአብሄር ቤት ለአምልኮ ሲመጡ ኢየሱስን አይተውና ከእርሱ ጋራ ተገናኘተው ለመሄድ ስለሆነ፤ በምንም መንገድ ሌላ ነገር ብንሰጣቸው ነፍሳቸውን ልናረካ እንደማንችል በመረዳት በተቻለን መንገድ ሁሉ ኢየሱስ የሚታይበትን መንገድ ብቻ እንድናመቻች ለማበረታታት፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ለአምልኮ ወደ በአሉ ከመጡት መሃል…ወደፊልጶስ መጥተው፣ ጌታው፤ እባክህን ኢየሱስን ለማየት እንፈልጋለን አሉት፡፡›› ዮሐ 12፡20-21

1. ዮሐ 12፡20-50 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ20-22 ለአምልኮ በመጡት የግሪክ ሰዎች ፊሊጶስ የተጠየቀው ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? የነዚህ ሰዎች ጥያቄ በማቴ 12፡38 ላይ ከምናያቸው በምን ይለያል? ለተጠየቀው ጥያቄ ፊሊጶስ የወሰደው እርምጃ ምንድነው?
2. ቁ23-24 ኢየሱስ እንደክብር አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው? ይህንን የኢየሱስ አነጋገር ከገላ 3፡13 ጋራ እንዴት ታስታርቀዋለህ? ስለስንዴ ቅንጣት በዚህ ክፍል የተናገረው ንግግር ከእርሱ ጋራ የሚገናኘው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡
3. ቁ27-33 ያለው ክፍል ኢየሱስ የሚያልፍበት ስሜት ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ሞክር፡፡ ቁ32 እንዴት ነው እርሱ ከፍ ከፍ ብሎ ሰውን ሁሉ ወደራሱ መሳብ የሚችለው? ኢየሱስ የተሰማውን ስሜት ወንድ ስለሆነ ሊደብቀው አልሞከረም፤ አንተስ ፍርሃት ሲሰማህ ፈራሁ፣ ሲጨንቅህ ተጨነቅሁ ማለት ትችላለህ ወይ?
4. ቁ34-36 ላይ ህዝቡ ከኢየሱስ ንግግር መሃል ጥያቄ የፈጠሩባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? የመልሱን አጠቃላይ ሃሳብ ስትመረምር ሊላቸው የፈለገው አንድ ነገር ምንድነው?
5. ቁ37-43 ኢሳይያስ ትንቢቱን የተናገረው ስለምን ዓይነት ሰዎች ነው? በሌላ በኩል ቁ42-43 ስለምን ዓይነት ሰዎች ነው የሚነግረን? ራሳቸውን ላለመግለጣቸው በምክንያትነት የተነገረው ምንድነው? ይህንን ሁኔታ ዮሐንስ ምን በማለት ይገልጠዋል? የነዚህን ሰዎች ችግር በአንተስ ላይ ታየዋለህ ወይ?
6. ቁ44-46 ኢየሱስ በአብና በወልድ መሃል ስላለው ግንኙነት የሚናገራቸው ሁለት እውነቶች ምንና ምንድናቸው?
7. ቁ47-50 የኢየሱስን ቃል በሚያቃልሉት ሰዎች ላይ በመጨረሻው ቀን የሚፈርደው ማን እንደሆነ ነው ከዚህ ክፍል የምንረዳው? ቃሉ ለምን እንደሚፈርድ ምክንያት ሆኖ የተነገረው ነገር ምንድነው?
8. በቁ20-22 ላይ ለምንድነው ለአምልኮ የመጡት ሰዎች ብዙ ሰው እያለ በኢየሱስ ላይ ብቻ ያተኮሩት? አንተስ ወደ እግዚአብሄር ቤት ለአምልኮ ስትሄድ ለማየት የምትፈልገው ኢየሱስን ወይስ ሌላ ልታየው የምትፈልገው ነገር አለህ? እኛ በቤቱ የምናገለግል አገልጋዮቹስ፣ ሰዎች ኢየሱስን ለማየት ወደቤቱ ሲመጡ የምናሳያቸው ማንን ይሆን? ሰዎች ማየትና ማወቅ የሚፈልጉት ኢየሱስን ስለሆነ ከእርሱ ሌላ የምናሳያቸው ነገር ለነፍሳቸው እርካታ ሊሰጣቸው ስለማይችል ልንጠነቀቅ ይገባናል፡፡

# ጥናት ሰላሳ አራት ዮሐንስ 13፡1-38

የጥናት ዓላማ፡- አንዳንዴ በማይገቡንና በማንረዳቸው ሁኔታዎች ውስጥ ጌታ እንድናልፍ ይፈቅድና፤ ቆይቶ ግን አሃ! ለዚህ ኖሯል ለካስ ያንጊዜ ያንን ያደረገው የምንልባቸውን ሁኔታዎች በህይወታችን ሊያመጣ እንደሚችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ኢየሱስም መልሶ የማደርገውን አሁን አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስተውላለህ አለው፡፡›› ዮሐ 13፡7

1. ዮሐ 13፡1-38 በአንድነት ይነበብ፡፡ ኢየሱስ ለሚወዳቸው ሙሉ ፍቅሩን የገለጠበት መንገድ ምን ነበረ? ቁ1-5 ላይ ኢየሱስ አወቀ በማለት የሚናገራቸውን ነገሮች በመዘርዘር ተናገር፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ሁሉ ነገሮች አወቀ ካለን በኋላ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? የክብር ሥፍራና ሥልጣን እንዳው እያወቀ እግር ለማጠብ መነሳቱ ምን ትምህርት ያስተምረናል?
2. ኢየሱስ በቁ8 ላይ ‹‹ካላጠብኩህማ ከእኔ ጋር እድል የለህም›› ሲል ምን ማለቱ ነው? በቁ9 ላይ ጴጥሮስ የኢየሱስን አነጋገር አልተረዳም ማለት የሚያስችለን ሃሳብ የትኛው ነው?
3. በቁ22-17 ላይ ኢየሱስ እንዲያደርጉት የሚያዛቸው ነገር ምንድነው? ለዚህስ የሚሰጣቸው ምክንያት ምንድነው? ቁጥር 17 በረከትን የሚያያይዘው ከምን ጋራ እንደሆነ ተናገር፡፡ አንተስ የምታውቀውና ጌታ ያስተማረህ ነገር ግን የማትፈጽመው ወይም የማትታዘዘው ነገር አለህ ወይ?
4. በቁ18-30 ‹‹ከመሆኑ በፊት አሁን ነገርኋችሁ፡፡›› የሚለው አነጋገር ስለኢየሱስ ማንነት የሚያስተምረን ነገር ምንድነው? እነዚህን ቁጥሮችንና ሌሎችንም በመጠቀም ኢየሱስ ይሁዳ አስቆሮቱን ከሌሎቹ ደቀመዛሙርት በተለየ ክፉ አይን እንደማያየው የምናውቅባቸው ምን ሁኔታዎችን መናገር ትችላለህ?
5. ቁ31-32 ላይ በብዙ የተጠቀሰው አንድ ቃል ምን የሚል ነው? ይህንን ክፍልና ዮሐ 17፡4-5ትን በማንበብ ኢየሱስ በሞቱ አብን የሚያከብረው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡ በማይመች መንገድ ስታልፍ በህይወትህ እግዚአብሄርን ለማክበር ምን ያህል ትዝ ይልሃል?
6. ደቀመዛሙርቱ በቁ34-35 ላይ ሊያስተምራቸው የፈለገው ነገር ምንድነው ትላለህ? በዚህ ክፍል መሰረት ኢየሱስን መውደዳችንን ወይም የእርሱ መሆናችንን ማሳየት የምንችልበት ዋነኛ መንገድ ምንድነው?
7. በቁ36-38 ጴጥሮስ ኢየሱስን መውደዱን ሊያሳይ የፈለገበት መንገድ ኢየሱስ በቁ35 ላይ ከሰጣቸው መመሪያ የምለይበትን መንገድ ተናገር፡፡ ጴጥሮስ በቁ34-35 ለተናገረው መሰረታዊ ነገር ብዙ ትኩረት እንዳልሰጠ የማይመስለው ለምንድነው? አንተስ ዋነኛውን ነገር ትተህ ዋነኛ ባልሆኑት ላይ ስታተኩር ራስህን ታገኘዋለህ ወይ?
8. መለስ ብለን ቁ6-7ትን ስናይ ጴጥሮስ እግሩን በኢየሱስ ለመታጠብ እንቢ ያለበት ምክንያት ለምንድነው? ለጴጥሮስ እንቢታ የኢየሱስ መልስ ምን ነበረ? አንተስ በህይወትህ ሳትረዳው ያለፍከበትና ቆይተህ ግን የእግዚአብሄርን ሃሳብ የተረዳህበት ነገር አለወይ? ዛሬ የምታልፍበት ነገር ባይገባህና ባትረዳውም፤ በእግዚአብሄር የሚገልጽበት የራሱ ጊዜ እንዳለው በማመን በእርሱ ላይ መደገፍ ትልቅ ጥበብ ነው፡፡

# ጥናት ሰላሳ አምስት ዮሐንስ 14፡1-31

የጥናት ዓላማ፡- ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደሚናገረው በኢየሱስ መምጣት የሚዘብቱና የሚያሾፉ ሰዎች የበዙበት ዘመን ቢሆንም፤ ኢየሱስ ግን ሥፍራን አዘጋጅቼላችሁ ተመልሼ መጥቼ እወስዳችኋለሁ እንዳለ፤ እንደቃሉ ተመልሶ እንደሚመጣን እንደሚወስደን በማሰብ እርስ በእርሳችን በዚህ ተስፋ እንድንበረታታ ለማሳሰብ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሄጄም ሥፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፤ እኔ ባለሁበት ከእኔ ጋራ እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ፡፡›› ዮሐ 14፡3

1. ዮሐ 14፡1-31 በአንድነት ይነበብ፡፡ በኢየሱስ መሄድ ልባቸው ያዘነውን ደቀመዛሙርቱን በቁ1-3 ላይ ያጽናናቸው ስለምን በመንገር ነው? ይህ የኢየሱስ የማጽናናት ዘዴ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በ2ኛ ተሰ 4፡17-18 ላይ ከመከራቸው ምክር ጋራ በማነጻጸር ተመሳሳይነት ወይም ልዩነታቸውን ለወገኖች አስረዳ፡፡
2. ቁ4-7 ስናነብ በዚህ ዘመን ብዙ ሰዎች ሊሰሙት የማይወዱት አንድ ወሳኝ የሆነ አነጋገር ኢየሱስ ሲናገር እናያለን፡፡ ይህ ሰዎችን የሚያስቆጣው ንግግር ምን ይመስልሃል? በአንተ አመለካከት ለምንድነው ሰዎች ይህንን አነጋገር ለመቀበል የሚያስቸግራቸው?
3. በቁ7-11 መሰረት አብን ልናውቅ የምንችለው በምን መንገድ ነው? ኢየሱስ አብን የገለጠበትን ደረጃ ዮሐ1፡14 እና ዕብ 1፡3 ምን በማለት ነው የሚናገሩት?
4. ቁ15-17 ላይ ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ የገባላቸው ትልቅ ተስፋ ምንድነው? ስለመንፈስ ቅዱስ ስራና ማንነት በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምታያቸውን እውነቶች ሁሉ ዘርዝር፡፡ ከዚህ ዝርዝር መሃል ለአንተ የበለጠ የምታደንቀውና ደስ የሚያሰኝህ የትኛው እንደሆነ ለወገኖች አካፍል፡፡
5. በቁ18-20 በተለይም በቁ18 ላይ የገባላቸው ተስፋ አዲስ ተስፋ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን? ወላጅ የሌላቸው ልጆች ሁኔታን አስመልክቶ የምታውቁትን ተነጋገሩበት፡፡ እነዚህን ቁጥሮች ስታነብ በአማኞች፣ በኢየሱስና እንዲሁም በአብ መሃል ሊኖር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?
6. ቁ21-24 ኢየሱስን መውደድ በምን እንደሚገለጥ ነው በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እየደጋገመ የተናገረው? ኢየሱስን ለሚወድ ሰው ስለሚያተርፈው ወይም ስለሚሆንለት ነገሮች ነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ቢያንስ አምስቱን ተናገር፡፡ አንተስ ኢየሱስን እወዳለሁ ስትል ቃሉን ለመጠበቅ ውሳኔ ከማድረግ ጋራ ነው ወይ?
7. የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አስመልክቶ በቁ15-17 ከተዘረዘረው ሌላ በቁ25-31 ውስጥ የምናያቸው ተጨማሪ ሥራዎቹ ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ኢየሱስ በሚሰጠውና አለም በምትሰጠው ሰላም መካከል ስለለው ልዩነት የሚገባህን ለወገኖች አስረዳ፡፡ ኢየሱስ የሚሰጠው ዓይነት ሰላም በአንተ ውስጥ ታያለህ ወይ?
8. በዚህ ክፍል ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለማጽናናት ከተናገራቸው ሃሳቦች ሶስቱን ጥቀስ፡፡ ለማጽናናት ከተናገራቸው መሃል በምዕራፍ 13 ውስጥ በብዙ ተደጋግሞ የተነገረው የትኛው ነው? ለአንተስ ህይወት በዚህ ዘመን ተደጋግሞ ቢነገርህ የምትፈልገው የትኛውን ይሆን? ጌታ ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አይተውህምና ተመልሶ መጥቶ እንደሚወስድህ በማሰብ እንደተሰሎንቄ ሰዎች በዚህ ተስፋ ተጽናና፡፡

# ጥናት ሰላሳ ስድስት ዮሐንስ 15፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር በህይወታችን ደስ እንዲሰኝና እናም ደስታችን እንዲበዛ የምንፈልግ ከሆነ፤ ትዕዛዙን በመጠበቅ በፍቅሩ ውስጥ መኖር ወሳኝነት እንዳለው ለማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እኔ የአባቴን ትዕዛዝ ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር፣ እናንተም ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ፡፡ ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህንን ነግሬአችኋለሁ፡፡›› ዮሐ 15፡10-11

1. ዮሐ 15፡1-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ክፈል ውስጥ ኢየሱስ ራሱንና አባቱን ቢዚህ ክፍል እንደምን አድርጎ ነው የሚያስቀምጥልን? በቁ1-2 ውስጥ ስንት አይነት ቅርንጫፎች ትመለከታለህ? ምንና ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ በመግረዝና በመቁረጥ መሃል ያለውን ልዩነት አስረዳ፡፡
2. ቁ3-4 ያተኮረበት ዋነኛ ሃሳብ ምንድነው ትላለህ? በዚህ ክፍል አነጋገር መሰረት ለክርስትያን ፍሬ ለማፍራትና ላለማፍራት ወሳኙ ነገር ምንድነው? ‹‹እናንተም በእኔ ካልኖራችሁ ፍሬ ልታፈሩ አትችሉም›› ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡
3. ቁ5-8ትን ስናነብ ደቀመዝሙር መሆናችንን የምንገልጽበት መንገድ ምንድነው? እግዚአብሄርን ለማክበር በዚህ ክፍል የተጠቀሰው አንደኛው መንገድ ምንድነው? ቁ2፣ ቁ5፣ ቁ8 እና ቁ16 ላይ ፍሬ ስለማፍራት ይናገራል፡፡ ይህ ፍሬ የሚለው ምን ዓይነት ፍሬን ነው የሚያመለክተን?
4. ቁ12-17 የኢየሱስ ወዳጅ የምንሆነው በእርሱ አነጋገር መሰረት ምን ብናደርግ ነው? ክፍሉን ስንመለከት እርሱ የሚያዘንና ራሱም በምሳሌነት ያሳየን ነገር ምንድነው? በአገልጋይና በወዳጅ መሃል ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ አስረዳ፡፡ ራስህን የምታየው እንደ አገልጋይ ወይስ እንደ ወዳጅ? ለምን?
5. ቁ18-21 አለም የክርስቶስን ተከታዮች ሊጠላ የሚችልባቸውን ቢያንስ አራት ምክንያቶች ተናገር፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በዚህ ክፍል ሊያስረዳቸው የፈለገው አንድ እውነት ቢኖር ምንድነው ትላለህ? አንተስ እንደ ክርስቶስ አማኝ ከዓለም ፍቅር መጠበቅ እንደሌለብህ ምን ያህል ገብቶሃል?
6. ቁ22-25 በማንበብ ኢየሱስን የተቃወሙትን ሰዎች አስመልክቶ ለሃጥያታቸው ምክንያት ሊያቀርቡ የማይችሉባቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው? እንደዚህ ያሉት ሰዎች ጥላቻቸው በማን በማን ላይ እንደሆነ ከቁ18-25 ያሉትን ቁጥሮች ተመልክተህ መልስ ስጥ፡፡
7. ቁ10-11 ተመልሰን ስናነብ የሚያበረታታን ምን እንድናደርግ ነው? ይህንን የማድረግ ውጤት ምንድነው? የደስታን ከህይወትህ መራቅ ከመታዘዝህ ጋራ አያይዘኸው ታውቃለህ ወይ? የተትረፈረፈ ደስታን በህይወትህ መለማመድ የምትችለው ትዕዛዙን ስትጠብቅና በፍቅሩ ውስጥ ስትኖር ብቻ መሆኑን አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ሰላሳ ሰባት ዮሐንስ 16፡1-33

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር አንዳንዴ የምንወደውንና መልካም የሆነውን ነገር ከህይወታችን ሲወስድ ከማዘን ይልቅ፤ የተሻለና የበለጠን ነገር ሊተካልን ሊሆን እንደሚችል ማሰብን እንደሚኖርብን ለመማር፡፡
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ይህንን በመናገሬም ልባችሁ በሃዘን ተሞልቷል፤ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ ይበጃችኋል፡፡ እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም፡፡›› ዮሐ 16፡6

1. ዮሐ 16፡1-33 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-4 ላይ ‹‹አስቀድሜ ይህንን የነገርኳችሁ›› የሚለው አነጋገር ስለኢየሱስ ማንነት ምን ያረጋግጣል? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ ስለተከታዮቹ እንደሚጠነቀቅ የሚያረጋግጥልህ የትኛው ሃሳብ ነው? ኢየሱስ የአንተ መሰናከል እንደሚገደው ይገባሃል ወይ?
2. ቁ5-11 ስንመለከት መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ዓለምን አስመልክቶ የሚያደርገው አንድ ነገር ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች መሰረት መንፈስ ቅዱስ በአማኞችና ባላመነ ሰው ውስጥ የሚሰራው ስራ የሚለየው በምን መንገድ እንደሆነ አስረዳ፡፡ ይህንን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በህይወትህ ምን ያህል ተለማምደሃል?
3. በቁ12-14 ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ስም ምን የሚል ነው? ቁ7 እና ቁ12-14 ትን በማንበብ መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት ከሚሰራቸው ነገሮች በዚህ ክፍል የሰፈሩትን ቢያንስ አራት ነገሮች ተናገር፡፡ ‹‹ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡›› ሲል ምን ይገባሃል?
4. በቁ16-18 ላይ ደቀመዛሙርቱን ግራ ያጋባው ወይም ጥያቄ የሆነባቸው ነገር ምን ነበረ? በአንተ አስተሳሰብ ኢየሱስ ይህንን ሲል ምን ማለቱ ነው ብለህ ታምናለህ?
5. ቁ19-24 ላይ ደቀመዛሙርቱ የሚያለቅሱበት፣ ነገር ግን ዓለም ሃሴት የሚያደርግበት ወቅት መቼ ነው? የደቀመዛሙርቱስ ሃዘን ወደ ደስታ የሚለወጥበት ወቅት መቼ ነው? ለመሆኑ የደቀመዛሙርቱን ጥያቄ ወደ ኢየሱስ ያቀረበው ሰው ማን ነው? አንዳንድ ጊዜ ጌታን ገና ሳትጠይቀው በውስጥህ ላለው ጥያቄህ መልስ ሆኖልህ ያውቃል ወይ?
6. በቁ26 ላይ ኢየሱስ ‹‹በዚያ ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ በእናንተ ፈንታ አብን እለምናለሁ ማለቴ አይደለም›› ማለቱ ምን ማለቱ ነው? ቁ25-28 ውስጥ አብ ደቀመዛሙርቱን የሚወድባቸው ሁለቱ ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው? አንተ ራስህ ምንም መካከለኛ ሳያስፈልግህ በኢየሱስ ስም አብን መለመን እንደምትችል ገብቶሃል ወይ?
7. በቁ33 ላይ ደቀመዛሙርቱ እንዲያውቁ የፈለገውና ያስጠነቀቃቸው ነገር ምን ነበረ? ለማበረታታት የተናገራቸውስ ሃሳብ ምንድነው? ይህንን ሁሉ ለደቀመዛሙርቱ ማለትም ከምዕ 14 ጀምሮ እስከ ምዕ 16 ያለውን ሁሉ ስለተናገረበት ምክንያት ቁ33 ምን ይነግረናል?
8. ቁ6-7 ትን ተመልሰን ስናይ የደቀመዛሙርቱ ልብ ለምንድነው በሃዘን የተሞላው? ኢየሱስ የእርሱን መሄድ የተሻለ እንደሆነ አድርጎ የሚነግራቸው ለምንድነው? የምትወደውና ካንተ እንዳይወሰድ የምታስበውን ነገር እግዚአብሄር ወስዶብህ ያውቃል ወይ? በተሻለ ነገር ህይወትህን ሊሞላ እንጂ ባዶ ሊያደርግህ ፈልጎ እንዳልሆነ በማመወቅ ልብህን ማረጋጋት ያስፈልግሃል፡፡

# ጥናት ሰላሳ ስምንት ዮሐንስ 17፡1-26

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ በምድር እያለ አብን እንዲያውቁት ማድረጉን በቂ አድርጎ ሳያይ፤ ወደፊትም እንዲያውቁህ አደርጋለሁ እንዳለ፤ እኛም እግዚአብሄርን ማወቅ የእድሜ ልክ ሥራችን እንደሆነ እንድንረዳ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እንዲሆን እኔም በእነርሱ እንድሆን፣ እንተን እንዲያውቁ አድርጌአለሁ፤ እንዲያውቁህም አደርጋለሁ፡፡›› ዮሐ 17፡26

1. ዮሐ 17፡1-26 በአንድነት ይነበብ፡፡ ‹‹ኢየሱስ ይህንን ከተናገረ በኋላ›› የሚለው ስለየትኛው ነግግሩ ነው የሚመልሰን? ቁ1-3 ትን ስናነብ ኢየሱስ ከአብ የተቀበለው ምን ዓይነት ስልጣን ነው? ኢየሱስ በዚህ ክፍል ውስጥ የዘለዓለም ህይወትን ምን በማለት ሲተረጉም ነው የምንመለከተው?
2. በቁ 4-5 ላይ ኢየሱስ ከአባቱ የተቀበለው ሥራ ምን ነበረ? ይህ ሥራ ተፈጽሟል ብለህ ታምናለህ ወይ? አልተፈጸመም ብለህ ካልክ ታዲያ ለምንድነው ኢየሱስ በዚህ ክፍል ‹‹የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርኩህ›› እያለ የሚናገረው?
3. ቁ6-9 መሰረት ደቀ መዛሙርቱን ከዓለም የሚለያቸው የወሰዷቸውን ቢያንስ አምስት እርምጃዎች ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል ስንመለከት ኢየሱስ እየጸለየ ያለው ስለማን ነው? ኢየሱስ ስለአንተ እንደሚገደውና እንደሚጸልይ ታውቃለህ ወይ?
4. ቁ10-13 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የኢየሱስ ጸሎቱ በምን ላይ ያተኮረ ነው ትላለህ? በተለይ ቁ10 በአብና በወልድ መካከል ስላለው አንድነት ምን ያስረዳናል? ኢየሱስ በአማኞች መሃል እንዲኖር ያሰበውን አንድነት እውን ለማድረግ በአንተ በኩል ምን ያህል ጥረት ታደርጋለህ?
5. ዮሐ 17፡8፣ ዮሐ 17፡14፣ 2ኛ ጢሞ 1፡13፣ 2ኛ ጢሞ 2፡2 በቅደም ተከተል ስንመለከት የምንረዳው አንድ እውነት ምንድነው? ቁ14-16 ላይ ስንመለከት የእግዚአብሄርን ቃል የተቀበለ ሰው ከዓለም ጋራ ስለሚኖረው ግንኙነት የሚያስተምረን ነገር ምንድነው? የአንተና የዓለም ግንኙነት ይህንን በተመለከተ ምን ይመስላል?
6. በቁ17-19 ላይ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን የሚልካቸው ወደየት ነው? ልክ ይህንን ተልዕኮ ከመስጠቱ በፊት አብን የሚለምነው ምን ብሎ ነው? ለተልዕኳቸው ይህ ምን አስተዋጽዎ አለው ብለህ ታምናለህ?
7. ከቁ20 ጀምሮ የሚጸልይላቸው ሰዎች ዓይነትና፤ አስቀድሞ በቁ1-19 የጸለየላቸው ሰዎች ዓይነት የሚለየው እንዴት ነው? ቁ20-23 ትን ስናነብ ኢየሱስ ለአማኞች የሰጠው ክብር እንደሆነ የተነገረው ነገር ምንድነው? በክፍሉ መሰረት ይህ ነገር በአማኞች መሃል ሊያመጣ የሚገባው ለውጥ ምንድነው?
8. በቁ24-26 በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄርን አንድ ጊዜ አውቀን የምንጨርሰው ነገር እንዳልሆነ የሚያስረዳን የትኛው ሃሳብ ነው? በእግዚአብሄር እውቀት እያደግህ ነው ወይ? እግዚአብሄርን ምንም ያህል እናውቀዋለን ብንልና እንዳወከውም ቢመስልህ፤ እርሱ ታውቆ የሚያበቃለት አምላክ ስላልሆነ እድሜ ልክህን ስለእርሱ መማር ተግባርህ ልታደርገው ይገባል፡፡”

# ጥናት ሰላሳ ዘጠኝ ዮሐንስ 18፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- ጴጥሮስ ኢየሱስ በተናገረው መሰረት መሸሽና ማምለጥ ሲገባው መገኘት በሌለበት ቦታ ተገኝቶ ራሱን ለሃጥያት እንዳጋለጠ፤ እኛም መጽሐፍ ቅዱስ ሽሹ ከሚለን ነገሮች መሸሽ እንጂ ተጋፍጦ ለማሸነፍ መሞከር ለሐጥያት እንደሚያጋልጠን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እነዚህ ይሂዱ ተውአቸው›› ዮሐ 18፡8 ‹‹ስምዖን ጴጥሮስና አንድ ሌላ ደቀመዝሙር ኢየሱስን ተከተሉት…በር ጠባቂዋም ጴጥሮስን አንተ ከዚህ ሰው ደቀመዛሙርት አንዱ አይደለህምን? አለችው፡፡ እርሱም አይደለሁም አለ፡፡›› ዮሐ 18፡15-17

1. ዮሐ 18፡1-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3 ስንመለከት ይሁዳ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ የነበሩበትን ሥፍራ ቀላሉ ማወቅ የቻለበት ምክንያት ምን ነበረ? ከይሁዳ ጋራ ኢየሱስን ለመያዝ የመጡት ማን ማን እንደነበሩ ዘርዝር፡፡ እነዚህ ሰዎች ይዘዋቸው የነበሩት ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
2. በቁ4-5 ላይ ኢየሱስን የሚፈልጉት ሰዎችና በ12፡20-21 ላይ ኢየሱስን ማየት በሚፈልጉት ሰዎች መሃል ያለው ልዩነት ምንድነው? አንተስ ኢየሱስን ማየት የምትፈልግበት ምክንያት ይኖርህ ይሆን?
3. ቁ4-8 ስናነብ ለጠየቁት ጥያቄ ‹‹እርሱ እኔ ነኝ›› ሲላቸው መሬት ላይ ሲወድቁ ይታያል፡፡ ራስህን በእነዚህ ሰዎች ሥፍራ አድርገህ ብታይ፤ እነርሱ እንዳደረጉት ዳግመኛ ጥያቄውን ለመጠየቅ ትደፍራለህ ወይ? ተወያዩበት፡፡ በመከራው ሰዓት እንኳን ለተከታዮቹ እንደሚገደው የሚጠቁምን የትኛው ክፍል ነው?
4. ቀያፋን በቁ12-14 ላይ ስንመለከተው በዚያን ጊዜ የነበረው ሃላፊነት ምን ነበረ? ይህ ሰው አይሁድን የመከረው ምን በማለት ነበረ? ይህ አነጋገሩ ምን መንፈሳዊ ትርጉም እንዳለው አስረዳ፡፡
5. በቁ19-24 ላይ ቀያፋ ኢየሱስን የጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች በምንና በምን ላይ ያተኮሩ ነበሩ? ለጥያቄዎቹ ኢየሱስ የሰጠው መልስ ምን ነበረ?
6. ኢየሱስ ለቀያፋ ለመለሰው መልስ ያስከተለበት ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስ ጥፊ ለመታው ሰው የመለሰው ምላሽ ምን የሚል ነው? ከኢየሱስ አመላለስ ለህይወታችን ልንማር የምንችለው አንድ እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
7. በቁ8 ላይ ተመልሰን ስንመለከት ደቀመዛሙርቱ ምን እንዲሆኑ ነበረ የተነገራቸው? በቁ16 ላይ ጴጥሮስ የሚያደርገው ድርጊት ኢየሱስ ከተናገረው ጋራ የሚቃረነው በምን መንገድ ነው? ይህንን ማድረጉ ያስከተለበት ነገር ምን ነበረ? አንተስ እግዚአብሄር ሽሽና አምልጥ በሚለው ነገር ላይ ለመጋፈጥ ትሞክር ይሆን? ሽሽ ከተባልከው ነገር መሸሽ እንጂ፤ ለመጋፈጥ መሞከር ትርፉ ራስህን ለሃጥያት ማጋለጥህ እንደሆነ ልትረዳ ያስፈልግሃል፡፡

# ጥናት አርባ ዮሐንስ 18፡28-19፡16

የጥናት ዓላማ፡- እነዚህ አይሁዶች እውነተኛው የፋሲካ በግ የሆነውን ኢየሱስን(1ኛ ቆሮ 5፡7) ለመግደል እየዶለቱ፣ በሌላ በኩል ግን የሃይማኖትን ስርዓት ለመፈጸም የሚያደርጉትን ጥረት በእግዚአብሄር ፊት ጸያፍ እንደሆነ፣ እኛም ከዚህ ዓይነት ግብዝ ሃይማኖታዊነት ልንጠነቀቅ እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አይሁድም ፋሲካን ለመብላት እንዲችሉ ላለመርከስ…እነርሱም ይህ ሰው ወንጀለኛ ባይሆን ኖሮ አንተ ፊት ባላቀረብነውም ነበር ብለው መለሱለት፡፡›› ዮሐ 18፡28-30

1. ዮሐ 18፡28-19፡16 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ28-32 ላይ ስናነብ አይሁድ በኢየሱስ ላይ እንዲፈርዱበት በሰጣቸው እድል ያልተጠቀሙት በምን ምክንያት ነው? ይህ ክፍል ደግሞ የሚሰጠን የተለየ ምክንያት ምን ትመለከታለህ?
2. ቁ33-35 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የጲላጦስ ጥያቄ ለኢየሱስ ምን የሚል ነው? ለጥያቄው ያገኘው መልስ ምን ነበረ? እያንዳንዱ ሰው በግሉ ስለ ነገስታት ንጉስና ስለ ጌቶቹ ጌታ ማንነት ለራሱ መልስ መስጠት ይኖርበታል፤ ታዲያ አንተስ ኢየሱስን ማን ትለዋለህ?
3. ከቁ33-39 ውስጥ በጲላጦስና በኢየሱስ መሃል የተካሄደው ውይይት ምንን አስመልክቶ ነው? በዚሁ ክፍል ውስጥ ጲላጦስ የማያውቀውና ከኢየሱስ ለመማር የጠየቀው ጥያቄ ምን ነበረ?
4. በቁ38-40 ላይ አይሁድ በኢየሱስ ላይ የሚያካሂዱትን የሃሰት ክስ ለማቆም ሌላ እድል ተሰጥቷቸው ነበረ ማለት የምንችለው ለምንድነው? ስለ ኢየሱስ‹‹በደል አላገኘሁበትም›› ስለ በርባን ደግሞ ‹‹በርባን ግን ወንበዴ ነበረ›› ተብሎ ተነግሯል፡፡ የሃይማኖት ሰዎች የሆኑት አይሁድ ከእነዚህ ሁለት ሰዎች ማለትም ከጻድቅና ከወንበዴ ምርጫቸው ማን እንዲሞት ነበረ? የሃይማኖት ሰው ሆነህ ከጽድቅ ይልቅ ለሃጥያት የምትቆምበት ጊዜ አለ ወይ?
5. 18፡38፣ 19፡4፣ 19፡6 ትን ስናይ የጲላጦስ አነጋገር በምን መንገድ ነው 2ኛ ቆሮ 5፡21 ላይ ያለውን እውነት የሚያረጋግጥልን?
6. ቁ7-12ትን ስናይ በአይሁድ አመለካከት ኢየሱስ የሞት ፍርድ የሚገባው በምን ምክንያት ነው? ሮሜ 13፡1 ላይ ካለው እውነት ጋራ የሚጣጣምና ኢየሱስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተናገረው ምን የሚለው ሃሳብ እንደሆነ ተናገር፡፡ በሥራ ላይ ያለው አለቃህ የእግዚአብሄር ሹም እንደሆነ ታምናለህ ወይ?
7. በቁ13 ሲጀምር ‹‹ጲላጦስም ይህን ሲሰማ…›› የሚለው አነጋገር የሚጠቁመው የትኛውን ሃሳብ ነው? አይሁድስ ለምን ይመስልሃል ይህንን ነገር ማንሳት የፈለጉት? የቄሳርን ወዳጅነት እንደሚፈልግና በደካማ ጎኑ እንደገቡበት፤ ጠላት የሚመጣብህ የአንተስ ደካማ ጎንህን አውቀህ ትጠነቀቃለህ ወይ?
8. ወደ ቁ28-30 ተመልሰን ስንመለከት አይሁድ ሲያደርጉ የሚታየው ጥንቃቄ ምን እንዳይሆን ነው? ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ለጠየቃቸው ጥያቄ መልሳቸው ምን ነበረ? እነዚህ ሰዎች በቁ28 ላይ የሚያደርጉት ድርጊት ግብዝነት የተሞላው ነው ማለት የሚቻለው ለምንድነው? የሰው ህይወት ለማጥፋት እየተሯሯጡ በሌላ በኩል እንዳይረክሱ እንደሚሞክሩት ሁሉ፤ አንተም በዚህ ዓይነቱ ግብዝነት እንዳትወሰድ ራስህን ጠብቅ፡፡

# ጥናት አርባ አንድ ዮሐንስ 19፡17-42

የጥናት ዓላማ፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ስቃይና ሞት በሰዎች የተጠነሰሰና በጲላጦስ ስልጣን ሥራ ላይ የዋለ ይምሰል እንጂ፤ እግዚአብሄር ራሱ ከዘለዓለም ያቀደውና የወሰነው ነገር እንደነበረ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ከዚያም ኢየሱስ ሁሉ ነገር እንደ ተፈጸመ አውቆ፣ የመጽሃፍ ቃል እንዲፈጸም ተጠማሁ አለ፡፡›› ዮሐ 19፡28

1. ዮሐ 19፡17-42 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ17-22 ላይ በጲላጦስና በአይሁድ መሃል አከራካሪ የነበረው ሃሳብ ምን ነበረ? ጲላጦስ በዚህ ስፍራ ያሳየው የአቋም ጥንካሬ ከዚህ በፊት ካሳየው አቋሙ የተለየ ሆኖ ይታይሃል ወይ? አስረዳ፡፡
2. ቁ23-24 በነዚህ ቁጥሮች ላይ ምን ያህል ወታደሮች ናቸው የሚታዩት? ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ ወታደሮቹ ያደርጉት የነበረው ነገር ምን ነበረ? እጀ ጠባቡን በእጣ ለመከፋፈል የወሰኑባቸው ከሰውና ከእግዚአብሄር አንጻር ምንና ምንድናቸው? ሰዎች ሳያውቁትና ሳይረዱት እንኳን የእግዚአብሄርን የዘላለም ሃሳብ እንደሚፈጽሙ ከዚህ መማር እንችላለን፡፡
3. በቁ25-27 የምታያቸውን ሰዎች ሁሉ ዘርዝር፡፡ ከእነዚህ መሃል ስንት ማርያሞች ታያለህ? ኢየሱስ ለሚወደው ደቀ መዝሙር ስለ እናቱ ስለ ማርያም የተናገረው ነገር ስለግንኙነታቸው የሚያረጋግጥልን ነገር ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ አንተስ ስለቤተሰብህ ያለህ አመለካከት እንደ ኢየሱስ የመንከባከብ ነው ወይ?
4. ወታደሮቹ በቁ24 ላይ የትንቢትን ቃል በመፈጸማቸውና፤ በቁ28 ላይ ኢየሱስ የትንቢትን ቃል በመፈጸሙ መሃል ያለው ትልቁ ልዩነት ምን ይመስልሃል? በቁ30 ላይ ኢየሱስ ‹‹ተፈጸመ›› ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ ነው ብለህ ታምናለህ?
5. በቁ31 ላይ አይሁድ ጲላጦስን የለመኑት ልመና ምን የሚል ነው? ይህንን ልመና የለመኑበት ምክንያታቸው ምን ነበረ? ኢየሱስ በማቴ 23፡24 ላይ የተናገረው አነጋገር የእነዚህን ሰዎች ድርጊት እንዴት እንደሚያንጸባርቅ አስረዳ፡፡ አንተስ ከዚህ ዓይነቱ እውርነት ህይወትህን ምን ያህል ትከላከለዋለህ?
6. ቁ32-36 ላይ አብረውት ከተሰቀሉት ሁለት ሰዎች የተለየ ነገር የተደረገበት ምን ታያለህ? የኢየሱስን ስቃይና መከራ ጸሃፊው በዝርዝር የሚነግረን ዋነኛው ምክንያት ለምንድነው? ኢየሱስን ጎን በጦር የወጋው ወታደር ሳያውቅና ሳይረዳ የፈጸማቸው ሁለት ትንቢቶች ምንና ምን ነበሩ?
7. ቁ38-42 በኢየሱስ ቀብር ላይ ዋነኛ ተሳታፊ ሆነው የምንመለከታቸው ሰዎች እነማን ናቸው? ሉቃ 23፡50-51 ስለ ዮሴፍ የሚነግረንን ነገሮች ዘርዝር፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች ኢየሱስን የተከተሉበት መንገድ የሚመሳሰለው በምን መንገድ ነው?
8. ቁ24፣ ቁ28፣ ቁ36 እና ቁ37 ‹‹የመጽሃፍ ቃል እንዲፈጸም›› የሚሉት አነጋገሮች ሁሉ ስለ ኢየሱስ ስቃይና ሞት ምን ያረጋግጡልናል? የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በጲላጦስና ሥልጣን የተወሰነ ነገር እንዳልሆነና፤ በእግዚአብሄር በራሱ ፐላንና እቅድ አስቀድሞ የተወሰነ ነገር እንደነበረ ከእነዚህና ከመሳሰሉት ክፍሎች እንረዳለን፡፡

# ጥናት አርባ ሁለት ዮሐንስ 20፡1-31

የጥናት ዓላማ፡- ቶማስ በደቀመዛሙርቱ መሃል አለመገኘቱ ኢየሱስን ማየት እንዳልቻለ ሁሉ፤ እኛም ከቅዱሳን ጉባኤ አለመገኘታችን ኢየሱስ በቅዱሳኑ መሃል ሊያደርግ ያለውን ድንቅ ነገር ከማየት እንደምንጎድል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው፡- ‹‹በዚህ ጊዜ ከአስራ ሁለቱ አንዱ የሆነው ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አልነበረም፡፡ ሌሎች ደቀመዛሙርትም ጌታን አየነው እኮ አሉት፡፡›› ዮሐ 20፡24-25

1. ዮሐ 20፡1-31 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ መግደላዊት ማርያም ወደ መቃብሩ ስለሄደችበት ሁኔታና ስላየችው ነገር ምን ይነግረናል? ምን ይመስልሃል ይህች ሴት የዚህ ዓይነቱን እርምጃ እንድትወስድ የገፋፋት? (ሉቁ 8፡2 ቢነበብ ይረዳል)፡፡ የመቃብሩን ባዶነት ስታይ የወሰደችው እርምጃ ምን ነበረ? ለሁለቱ ደቀመዛሙርት የሰጠችው መረጃ ልክ ነበረ ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
2. በቁ3-7 ላይ የተካሄደውን ትዕይንት በአጭሩ ተናገር፡፡ ጴጥሮስ ወደ መቃብሩ ውስጥ በመግባቱ ከሌላኛው ደቀ መዝሙር የተለየ የተመለከተው ነገር ምን ነበረ? በዚህ ክፍል ዮሐንስ ከጴጥሮስ፤ ጴጥሮስ ደግሞ ከዮሐንስ ተሽለው የተገኙበትን ነገር ተናገር፡፡
3. ዮሐንስ በቁ8-9 ላይ ወደ መቃብሩ መድረስ ብቻ ሳይሆን ወደ ውስጥ ገብቶ መመልከቱ ምን ሲጠቅመው ታያለህ? እነዚህ ቁጥሮች የኢየሱስን ትንሳኤ አስመልክቶ ደቀመዛሙርቱ ስለነበሩበት ሁኔታ ምን ይነግረናል?
4. በቁ10-18 ላይ ማርያም በነበረችበት ስፍራ በመቆየቷ ያተረፈችው ነገር ምን ታያለህ? ማርያም በኢየሱስ የተጠየቀቻቸው ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን ነበሩ? ዛሬ አንተስ የምትፈልገው ገንዘብ ወይስ ክብር ወይስ ዝና ውይስ ኢየሱስን ትፈልገዋለህ?
5. በቁጥር 19-23 ላይ የተፈጸመ ምን ተአምር ታያለህ? የኢየሱስ መገኘት በደቀመዛሙርቱ ልብ ውስጥ የፈጠረው ስሜት ምን ነበረ? ለምንድነው ብለህ ታምናለህ ይህ ዓይነቱ ስሜት በደቀመዛሙርቱ ውስ የተከሰተው? ሁኔታዎች ዝግትግት ያሉብህና ኢየሱስ ደርሶ ደስ ያሰኘህ ጊዜ ካለ ለወገኖች አካፍል፡፡
6. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› ካለ በኋላ ያደረገው ነገር ምንድነው? ለሁለተኛ ጊዜ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› ካለ በኋላ ያደረገውስ ነገር ምንድነው? ሰላምን ለደቀመዛሙርቱ ሁለት ጊዜ ማወጁ በአንተ አመለካከት ምን ትርጉም እንዳለው አስረዳ፡፡
7. ቁ30-31 ኢየሱስ በደቀመዛሙርቱ ፊት ካደረጋቸው ድንቅ ምልክቶች መሃል ዮሐንስ ምን ያህሉን ነው በወንጌሉ ውስጥ ያላሰፈረልን? የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበት ዋነኛ አላማው ምንድነው? በአንተ ህይወት ውስጥ የዮሐንስ ዓላማ ተፈጻሚ ሆኗል ብለህ ከሙሉ ልብህ ታምናለህ ወይ?
8. ቁ24-25 ቶማስ ባለመገኘቱ ያመለጠው ነገር ምን ነበረ? ቁ26-29 ቶማስ በቅዱሳን ጉባኤ በመገኘቱስ ያተረፈው ነገርስ ምን ነበረ?

# ጥናት አርባ ሶስት ዮሐንስ 21፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- የዮሐንስን መጨረሻ ለማወቅ በመሞከሩ ጴጥሮስ በኢየሱስ እንደተገሰጸ ሁሉ፤ እኛም በሰዎች ህይወት ላይ ከማተኮር ይልቅ እግዚአብሄር ለራሳችን የሰጠንን ሃላፊነትና አገልግሎት በመወጣት ላይ ማተኮር እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው፡- ‹‹ጴጥሮስ ባየው ጊዜ ጌታ ሆይ እርሱስ? ብሎ ጠየቀ፡፡ ኢየሱስም እስከመለስ ድረስ በህይወት እንዲኖር ብፈልግ እንኳ አንተን ምን ቸገረህ? አንተ ራስህ ተከተለኝ አለው፡፡›› ዮሐ 21፡21-22

1. ዮሐ 21፡1-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3 ላይ በመሪነት ደረጃ የምናየው ሰው ማን ነው? ይህ ሰው ስንት ተከታዮች ነበሩት? እነዚህ ሰዎች ያደጉበት ስራ ሆኖ እያለ ሌሊቱን ሁሉ ምንም አለመያዛቸው ከዮሐ 15፡5 ምን መማር ይችላሉ ትላለህ? ለአንተስ ከዚህ ምን መንፈዊ ትምህርት ትማራለህ?
2. ቁ4-6 ደቀመዛሙርቱ ምንም አሳ እንደሌላቸው ሲነግሩት ኢየሱስ ያዘዛቸው ትዕዛዝ ምን ነበረ? ኢየሱስ መሆኑ እንዳላወቁ ክፍሉ ይነግረናል፤ ታዲያ ለምን ይመስልሃል የማያውቁት ሰው የነገራቸውን ለመስማትና ለመታዘዝ ክፍት የሆኑት?
3. ቁ7-11 ላይ ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር ጌታ መሆኑን መረዳት ያወቀበት ምክንያት ምን ይመስልሃል? ቁ11 ላይ ‹‹ይህንን ያህል ቢያዝም መረቡ አልተቀደደም›› የሚለው አነጋገር በወንጌል ነፍሳትን ለምናጠምድ ሰዎች ምን መንፈሳዊ ትምህርት ሊኖረው እንደሚችል አስረዳ፡፡
4. ቁ12-14 ሲደክሙና በከንቱ ሲለፉ ለነበሩት ደቀመዛሙርቱ የተናገራቸው አንድ ነግር ምን ነበረ? ከንግግሩ በኋላ ጌታ ያደረገው ድርጊት ምን እንደነበረ አስረዳ፡፡ ሞክረው ሞክረው ላልተሳካላቸውና ለዛሉት ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ሲያደርግ ያየነው ነገር ለአንተስ ህይወት ምን ተስፋ ይሰጥሃል?
5. ቁ15-17 የኢየሱስ ጥያቄና የጴጥሮስ መልሶች በሙሉ በምን ላይ ያተኮሩ ነበሩ? ከጴጥሮስ መልስ በኋላ ኢየሱስ በማስከተል የተናገራቸው ነገሮችስ ትኩረታቸው ምን ነበረ? በአንተ አመለካከት በፍቅርና በሃላፊነት መሃል ያለው ግንኙነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ሃላፊነትህን የምትወጣው ከፍቅር ይሆን ወይስ ከግዴታ?
6. በቁ19 እና በፊሊ 1፡20 መካከል ስላለው መመሳሰልና ሁለቱ ክፍሎች ሊያስተምሩን የሚችሉትን አንድ እውነት ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
7. ቁ20-25ት ላይ ስናነብ ዮሐንስ ኢየሱስ እስከሚመጣ ድረስ አይሞትም የሚለው ወሬ የተነሳው እንዴት ነው? ሰዎች የተናገሩትን በትክክል ለመረዳት ጊዜ ሳይወስዱ ያልተጨበጠ ወሬን ማውራት በአካባቢህ ምን ያህል ችግር ነው ብለህ ታምናለህ? ለዚህ አይነቱ ችግርስ መፍትሄው ምንድነው ትላለህ?
8. ቁ20-22 ጴጥሮስ ከራሱ አልፎ በተጨማሪ ማወቅ የፈለገው ስለማን ነበረ? አንተስ ከራስህ ይልቅ የሰዎችን የህይወት አቅጣጫ ለማወቅ የሞከርክበት ጊዜ አለ ወይ? እግዚአብሄር ለራስህ ባቀደው ጎዳና ላይ መራመድ እንጂ የለሎችን አገልግሎትና የኑሮ አቅጣጫ ለማወቅ ጊዜ ማጥፋት እንደማይኖርብህ ከኢየሱስ ተማር፡፡